# የራስን ሥነ-መለኮት መገንባት

## ትምህርት 2

## የክርስቲያን ሥነ-መለኮትን ማሰስ

Manuscript

thirdmill
Biblical Education. For the World. For Free.

© 2019 by Third Millennium Ministries

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ ከአሳታሚው የጽሑፍ ፈቃድ ውጭ ማጠቀሻነት፣ ለግምገማ ፣ ለአስተያየት ወይም ለትምህርት ዓላማዎች በአጭሩ መጠቀም ካልሆነ በስተቀር የዚህ ጽሑፍ ክፍል በማንኛውም መልኩ ወይም በማንኛውም መንገድ ለትርፍ ሊባዛ አይችልም። የአሳታሚው አድራሻ Third Millennium Ministries, Inc., 316 Live Oaks Blvd., Casselberry, Florida 32707.

በሌላ መንገድ ካልተጠቆመ በስተቀር ፣ ሁሉም የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች በ1954 ዓ.ም ከታተመው መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው።

## ስለሴርድሚል

እ.ኤ.አ. በ 1997 የተቋቋመው ፣ ሴርድሚል ለትርፍ ያልተቋቋመ የወንጌላዊ ክርስቲያናዊ አገልግሎት ሲሆን

**መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት፣ ለዓለም፣ በነጻ ይሰጣል፡፡**

ግባችን በዓለም ዙሪያ በሙቶ ሺዎች ለሚቆጠሩ ፓስተሮች እና ለአገልግሎት በቂ ሥልጠና ለሌላቸው የክርስቲያን መሪዎች ነፃ የክርስትና ትምህርት መስጠት ነው። በእንግሊዝኛ ፣ በአረብኛ ፣ በማንዳሪን ፣ በሩሲያኛ እና በስፓኒሽ ተወዳዳሪ የሌለውን የመልቲሚዲያ ሴሚናሪ ሥርዓተ ትምህርት በማዘጋጀት እና በዓለም አቀፍ ደረጃ በማሰራጨት ይህንን ግብ እያሟላን እንገኛለን። በአጋር መሥሪያ ቤቶቻችን አማካኝነት ሥርዓተ ትምህርታችን ከአሥር በላይ በሚሆኑ ሌሎች ቋንቋዎችም እየተተረጎመ ነው። ሥርዓተ ትምህርቱ በጥሩ ግራፊክ የተሠሩ ቪዲዮዎችን፣ የታተሙ ትምህርቶችን እና የበይነመረብ ግብዓቶችን ያካትታል። በትምህርት ቤቶች ፣ በቡድኖች እና በግለሰቦች ፣ በበይነመረብም ሆነ በትምህርት ማህበረሰቦች ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውል የተቀየሰ ነው።

ባለፉት ዓመታት፣ እጅግ በጣም ጥሩ ይዘትን እና ጥራትን የተሸለሙ የመልቲሚዲያ ትምህርቶችን ለማምረት ከፍተኛ ወጪ ቆጣቢ ዘዴን አዘጋጅተናል። ጸሐፊዎቻችን እና አርታኢዎቻችን በስነ-መለኮት የሰለጠኑ አስተማሪዎች ፣ ተርጓሚዎቻችን የሥነ-መለኮታዊ አስተውሎት ያላቸውና የሚተረጉሙበት ቋንቋዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የሆናቸው ናቸው ፣ እንሁም ትምህርቶቻችን ከዓለም ዙሪያ የመጡ በመቶዎች የሚቆጠሩ የተከበሩ የሴሚናሪ ፕሮፌሰሮች እና ፓስተሮች አሳቦችን ይዘዋል። በተጨማሪም ፣ የእኛ ግራፊክ ዲዛይነሮች ፣ ሥዕላዊ መግለጫዎች እና አዘጋጆች ዘመናዊ መሣሪያዎችን እና ቴክኒኮችን በመጠቀም ከፍተኛውን የዝግጅት ደረጃዎችን የሚያሟሉ ናቸው፡፡

የስርጭት ግቦቻችንን ለማሳካት ፣ ሴርድሚል ከቤተክርስቲያናት ፣ ከሴሚናሪዎች ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ፣ ከሚሲዮናውያን ፣ ከክርስቲያን ማሰራጫዎች እና ከሳተላይት ቴሌቪዥን አቅራቢዎች እና ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ስትራቴጂካዊ አጋርነት ፈጥሯል። እነዚህ ግንኙነቶች ቀደም ሲል ስፍር ቁጥር የሌላቸው የቪዲዮ ትምህርቶችን ለአገሬው ተወላጅ መሪዎች ፣ ለፓስተሮች እና ለሴሚናሪ ተማሪዎች ማሰራጨት አስችሏል። የድረ-ገጾቻችን እንዲሁ እንደ ስርጭት መንገዶች ሆነው ያገለግላሉ እንዲሁም የመማሪያ ማህበረሰብ እንዴት እንደሚጀምሩ ግብዓቶቸንና ትምህርቶቻችንን ለማግኘት ተጨማሪ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡

ሴርድሚል በ IRS እንደ 501 (ሐ) (3) ኮርፖሬሽን እውቅና ተሰጥቶታል። እኛ ገቢ የምናገኘው ከአብያተ-ክርስቲያናት ፣ ፋውንዴሽንስ፣ ንግድ ተቋማት እና ግለሰቦች በሚሰጡት እርዳታ ነው፡፡ ሰዎች ለእኛ ሲለግሱ ከሚከፍሉት ግብር ይቀነስላቸዋል፡፡ ስለአገልግሎታችን ተጨማሪ መረጃ ፣ እና እርስዎ እንዴት መሳተፍ እንደሚችሉ ለማወቅ ፣ እባክዎ www.thirdmill.org ን ይጎብኙ።

# የራስን ሥነ-መለኮት መገንባት

## ትምህርት ሁለት

## የክርስቲያን ሥነ-መለኮትን ማሰስ

## ማውጫ


| | |
|---|---|
| መግቢያ | 1 |
| የክርስትና ሥነ-መለኮት | 1 |
| ከትርጓሜዎች ጋር የተያያዙ ችግሮች | 1 |
| አማራጭ ፍቺ | 3 |
| አንድነት በልዩነት | 5 |
| የተዋሃደ ሥነ -መለኮት | 6 |
| የሥነ-መለኮት ብዝኃነት | 7 |
| ክርስቲያናዊ ትውፊቶች | 10 |
| የክርስቲያናዊ ትውፊት ትርጓሜ | 10 |
| አሉታዊ ትርጓሜ | 10 |
| አዎንታዊ ትርጓሜ | 11 |
| የትውፊት ዝንባሌዎች | 12 |
| ኦርቶዶክሳዊነት | 13 |
| ኦርቶፓቶስ | 14 |
| የትውፊት አስፈላጊነት | 15 |
| ራሳችንን ለማወቅ | 15 |
| ሌሎችን መገንዘብ | 16 |
| የተሐድሶው ትውፊት/ወግ | 17 |
| ታሪካዊ አመጣጡና ዕድገቶቹ | 18 |
| ዝንባሌዎች | 19 |
| አምስቱ ብቻዎች | 20 |
| የቅዱሳት መጻሕፍት አንድነት | 21 |
| ስለእግዚአብሔር ያለው አስተምህሮ | 23 |
| ማጠቃለያ | 26 |
| አስተዋፅዖ አድራጊዎች | 27 |

# የራስን ሥነ-መለኮት መገንባት

## ትምህርት ሁለት

## የክርስቲያን ሥነ-መለኮትን ማሰስ

## መግቢያ

ወጣት ባለትዳሮች በሚጋቡበት ጊዜ ብዙውን ጊዜ ከቤተሰቦቻቸው የመነጩ ልዩነቶችን መቋቋም አለባቸው። እርስ በርሳቸው በጥልቅ ሊዋደዱ ይችሉ ይሆናል ፣ ነገር ግን በሕይወታቸው ለየትኛው ነገር ቅድሚያ መስጠት እንደሚገባቸውና በሚጠብቁት ነገር ላይ ምን ያህል ተጽዕኖ እንዳሳደሩባቸው ማወቅ አለባቸው። ይህንን እውነታ ካላወቁ ፣ ክርስቶስ የሚፈልገውን ዓይነት የፍቅር እና መከባበር ያለበት የጋብቻ ግንኙነት መገንባት ከባድ ሊሆን ይችላል።

የክርስቶስ ተከታዮች ሥነ-መለኮትን ሲመረምሩ በብዙ መልኩ ተመሳሳይ ነገር ይሆናል። ክርስቲያኖች ከባህሎቻቸው፣ ከንዑስ ባህሎቻቸው እና ከተለያዩ የቤተክርስቲያን ክፍሎች ወጎች የመነጩ የተለያዩ ቅድሚያ የሚሰጣቸው እና የሚጠበቁ ነገሮች አላቸው። እኛ የክርስትናን ሥነ -መለኮት ስናጠና እና ስለምንኖር እነዚህ ዳራዎች እኛ ቅድሚያ በሚንሳጣቸውን በምንጠብቃቸው ነገሮች ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ተጽዕኖዎች በእኛ ላይ ምን ያህል ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ካላወቅን ፣ ክርስቶስ የሚፈልገውን የፍቅር እና የአክብሮት ሥነ -መለኮታዊ አመለካከቶችን መገንባት አስቸጋሪ ይሆናል።

በሥነ -መለኮት ግንባታ ተከታታይ ትምህርቶች ውስጥ ይህ ሁለተኛው ትምህርት ነው። በዚህ ትምህርት ውስጥ ፣ ይህንን አጠቃላይ ጥናት የሚመራውን መሰረታዊ አቅጣጫዎችን እናዘጋጃለን። ይህንን ትምህርት "የክርስትና ሥነ -መለኮትን ማሰስ" የሚል ርዕስ ሰጥተነዋል፡፡ የተለየ የክርስትና ሥነ -መለኮትን እንዴት ማዳበር እንደሚቻል ስንመረምር የሚመራንን አንዳንድ በጣም አስፈላጊ ቅድመ -ግምቶችን እናዘጋጃለን።

ከሰፊው ወደ ጠባብ ጉዳዮች በመሸጋገር ይህንን ርዕሰ ጉዳይ በሦስት መንገዶች እንመለከታለን። በመጀመሪያ ፣ በክርስትና ሥነ -መለኮት ላይ ያለንን አመለካከት እንገልፃለን - ክርስቲያን ሥነ-መለኮት ምን ዓይነት ሥነ-መለኮት ነው? ሁለተኛ የተወሰኑ የክርስትና ወጎች ለክርስቲያናዊ ሥነ -መለኮት እንዴት ቅርፅ እንደሚሰጡ እንመረምራለን። ሦስተኛ የተወሰኑትን የተሐድሶ ትውፊት መሰረታዊ መርሆችን እንመለከታለን - እነዚህን ትምህርቶች ያካተተ የክርስትና እምነት የተወሰነ ክፍል እናያለን። በመጀመሪያ ወደ አንድ የክርስትና ሥነ -መለኮት አጠቃላይ ሀሳብ እንሸጋገር። በእነዚህ ትምህርቶች ውስጥ ይህን ቃል ስንጠቀም ምን ማለታችን ይሆን?

## የክርስትና ሥነ-መለኮት

ምንም እንኳን ብዙ ጊዜ ስለ "ክርስቲያናዊ ሥነ -መለኮት" ብንናገርም ፣ የዚህ አገላለጽ ትርጉም ሙሉ በሙሉ ግልፅ አይደለም። አንዳንድ ሰዎች የክርስትናን ሥነ-መለኮት ክርስቲያኖች በትክክል የሚያምኑትን እምነት እንደሆነ ያስባሉ። ነገር ግን ብዙ ክርስቲያኖች በትክክል ክርስቲያናዊ ያልሆኑ ነገሮችን እንደሚያምኑ ሁላችንም እናውቃለን። ሌሎች ሰዎች ደግሞ ክርስቲያናዊ ሥነ-መለኮት ክርስቲያኖች ማመን የሚገባቸውን የያዘ እንደሆነ ይናገራሉ። ግን እኛ ማመን በሚገባን ላይ ሁል ጊዜ እንደማንስማማ መቀበል አለብን። በእነዚህ እና መሰል ውስብስብ ነገሮች ምክንያት "የክርስትና ሥነ -መለኮት" የሚለውን ቃል ስንጠቀም በዚህ ተከታታይ ትምህርት ውስጥ ምን ማለታችን እንደሆነ ግልፅ ማድረግ አለብን።

ሦስት ጉዳዮችን እንዳስሳለን - በመጀመሪያ ፣ ለክርስቲያናዊ ሥነ -መለኮት ትርጓሜዎችን ከመፍጠር ጋር የተያያዙ አንዳንድ ችግሮችን እንመለከታለን። ሁለተኛ ፣ የክርስትና ሥነ -መለኮትን አማራጭ ፍቺ እናቀርባለን። ሦስተኛ ፣ የክርስትና ሥነ -መለኮት የሚያካትተውን አንድነት እና ልዩነት እናስተውላለን። የክርስትናን ሥነ -መለኮት ለመግለፅ ስንሞክር በመጀመሪያ ያጋጠሙንን አንዳንድ ችግሮች እንመልከት።

### ከትርጓሜዎች ጋር የተያያዙ ችግሮች


ካጋጠሙን ታላላቅ ችግሮች አንዱ የክርስትናን ሥነ-መለኮት ክርስቲያናዊ ካልሆኑ ሥነ-መለኮት ለመለየት የምንጠቀምባቸው መንገዶች ናቸው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ልዩነቶቹን ለማየት አስቸጋሪ አይደሉም ፣ ግን ብዙ ጊዜ የክርስትናን ሥነ -መለኮት ከሌላ ሥነ -መለኮት ለመለየት እጅግ በጣም ከባድ ነው። ከሌሎች የዓለም ታላላቅ ሃይማኖቶች ጎን ለጎን ክርስትናን ስናስብ ፣ ከክርስትና እምነቶች በቀላሉ የሚለዩ በርካታ ሥነ-መለኮቶች አሉ። ለምሳሌ አንዳንድ ሰዎች ክርስትናን እና

ሂንዱዝምን ለማዋሃድ ቢሞክሩም ፣ የሂንዱይዝም ብዙ አማልክት ከክርስቲያናዊ እምነት በጣም የተለየ ያደርገዋል። ከአንድ አምላክ አምልኮ ይልቅ የብዙ አማልክት አምልኮ መከተል ሁለቱን አንድ እንዳልሆኑ ግልጽ ያደርጓል።

በሌላ በኩል እስልምና ወደ ክርስትና በጣም ይቀርባል። ልክ እንደ ክርስትና ፣ እስልምና ታሪካዊ አመጣጡን ከአብርሃም ጋር ያያይዛል፡፡ ከዚህ በላይ የእስልምና ነቢይ እና ተከታዮቹ ቁርአንን ሲፈጥሩ ከክርስቲያናዊ ትምህርቶች ጋር ግንኙነት ነበራቸው፡፡ ስለዚህ ፣ በክርስትና እና በእስልምና መካከል በርካታ መመሳሰሎች አሉ። አሁንም ፣ በአብዛኛው ፣ እስልምናን ከክርስትና እምነት ለመለየት ትልቅ ችግር የለብንም ምክንያቱም በመካከላቸው ግልፅ እና መሠረታዊ ልዩነቶች አሉ። ለምሳሌ ፣ ክርስትና የክርስቶስን አምላክነት እና የበላይነት ያረጋግጣል ፤ ነገር ግን እስልምና እነዚህን እውነቶች ይክዳል።

የአይሁድ እምነትስ? የአይሁድ እምነት ይበልጥ ከክርስትና ጋር በቅርበት የተሳሰረ እና ተመሳሳይ ነው፤ ምክንያቱም ክርስትና ያደገው ከአይሁድ እምነት ነው። የሆነ ሆኖ ፣ የአይሁድ እምነት ኢየሱስ መሲሕ ፣ ክርስቶስ መሆኑን ስለሚክድ ፣ ከክርስትና እምነት ጋር የሚያምታቱት በጣም ጥቂት ሰዎች ናቸው። የእነዚህ እና የሌሎች ዋና ዋና የዓለም ሃይማኖቶች ሥነ - መለኮታዊ አመለካከቶች ከክርስቲያናዊ ሥነ -መለኮት በጣም የተለዩ በመሆናቸው ብዙ ሰዎች እነርሱን ለመለየት ብዙም አይቸገሩም። በእኛ ሥነ -መለኮት እና በእነርሱ መካከል ጠንካራ የሚባሉ ድንበሮችን ማቋቋም እንችላለን።

ከሥነ-መለኮት አንጻር ክርስትናን ከአይሁድ እምነት እና ከእስልምና የሚለየው ፣ በእርግጥ ፣ አንዱ ትኩረት ስለ ክርስቶስ ስብዕና ነው። ሁሉም ሃይማኖቶች የእምነት አስተሳሰብ አላቸው፡፡ እነዚያ ሌሎች ሃይማኖቶች ፣ በእርግጥ - የአይሁድ እምነት እና እስልምና - እኛ በክርስትና እንደምንለው በእግዚአብሔር ስለማመን ያወሳሉ፡፡ እኔ እንደማስበው ፣ ያ ለእኛ የተለየ ነው ፣ ከአይሁድ እምነት እያደገ ፣ እግዚአብሔር የገባውን ቃል የሚጠብቅ ነው... በክርስትና ውስጥ ክርስቶስ የእነዚህ ቀደምት




ክርስቲያናዊ ሥነ-መለኮትን ከሌሎች ሥነ-መለኮቶች መለየት አለብን

ተስፋዎች ሁሉ ፍፃሜ ይሆናል። እርሱ በእርግጥ ሰዎችን ከኃጢአታቸው የሚያድነው መሲሕ ነው፡፡ እርሱ መስዋዕት ሆኖ ሕይወቱን ለእኛ መስጠት ብቻ ሳይሆን በእርሱ አማካኝነት እኛ መዳን፣ ጽድቅና ይቅርታ እንዲሆንልን መንገድ ሆኖልናል፡፡

— ዶ/ር ኦሊቨር ኤል ትሪሜው ፣ ጁኒየር

በተመሳሳይ ፣ ብዙ የስነ-መለኮት ትምህርት ቤቶች የክርስትና እና የክርስትና ያልሆነ አስተሳሰብን ያዋህዳሉ ፣ ከዚህም የተነሣ አንዳንድ ጊዜ እውነተኛ ክርስትናን ከሌሎች እምነቶች ለመለየት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ በዘመናችን እንዲህ ዓይነቱን ቅይጥ አስተሳሰብ ማየት በታዋቂ የክርስቲያን የአምልኮ ኑፋቄዎች ለምሳሌ እንደ የይሖዋ ምሥክሮች ፣ ሞርሞኒዝም እና የክርስትና ሳይንስን ውስጥ እናያለን። እንዲያውም ብዙ አብያተ ክርስቲያናት የቀድሞ አያቶቻቸውን ሥነ -መለኮታዊ አቋም ትተው በዘመናዊው ሊበራሊዝም ውስጥ ገብተዋል። አሁን ፣ የእነዚህ ቅይጥ ሃይማኖቶች አንዳንድ ገጽታዎች ክርስቲያን ያልሆኑ

እንደሆኑ በቀላሉ ተለይተዋል ፣ ግን ሌሎች አካላት ለእውነተኛ ክርስትና በጣም ቅርብ ናቸው። በዚህ ምክንያት ፣ በእነዚህ አጋጣሚዎች በክርስትና እና ክርስትና ባልሆኑ የሃይማኖት ትምህርቶች መካከል ግልጽ መስመሮችን ለመሳል እንቸገራለን።

ይባስ ብሎ በክርስቶስ ታማኝ አማኞች መካከል ስለ ሥነ-መለኮታዊ ገጽታ አስቡ። በእውነተኛ ክርስትና ክፍል ውስጥ እንኳን ፣ ከክርስቲያናዊ ሥነ-መለኮት ይልቅ ስለ ክርስቲያናዊ ሥነ -መለኮቶች - በብዙ ቁጥር - መናገር ይቀላል። በጣም ብዙ የተለያዩ የክርስትና ዓይነቶች አሉ ፣ ስለዚህ ከእነዚህ ሁሉ ብዙ የክርስትና ዓይነቶች የትኛው እውነተኛ ተደርገው መታየት እንዳለበት ሁሉንም ሰው በሚያረካ መልኩ መለየት አይቻልም። እውነተኛው የክርስትና ሥነ -መለኮት የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትን ትምህርት ያካትታል? ስለ ሮማ ካቶሊክ ትምህርቶችስ? ንፁህ የፕሮቴስታንት እምነት ክፍል የቱ ነው - አንግሊካን? መጥመቃውያን? ሉተራን? ሜቶዲስት? ፕሬስባይቴሪያን? እያንዳንዱ የቤተክርስቲያን ክፍል ማለት ይቻላል የተለያዩ የክርስትና ክፍሎችን ትክክለኛነት በራሱ መንገድ ይገመግማል። እያንዳንዱ ክፍል ማለት ይቻላል ሥነ-መለኮቱ ከሁሉም ይልቅ ትክክለኛ ስራት እንደሆነ ያምናል። ስለእነዚህ ክርስቲያናዊ የውስጣዊ አለመግባባቶች ስናስብ ፣ "የክርስትና ሥነ -መለኮትን" በትክክል መግለፅ የበለጠ ከባድ ይሆናል።

በዚህ መንገድ አስቡት - እንደ ክርስቲያን ለመቁጠር ሰዎች ሊያምኑባቸው የሚገቡትን ትምህርቶች ሁሉ በመጻፍ የክርስትናን ሥነ -መለኮት ከሌሎች የዓለም ሥነ -መለኮታዊ ሥርዓቶች ለመለየት ቢትጠየቁስ? ኢየሱስ ጌታ ነው; ኢየሱስ አዳኝ ነው; ኢየሱስ ብቸኛው የመዳን መንገድ ነው ሊትሉ ትችላላችሁ። ኢየሱስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ; ኢየሱስ ከሞት ተነስቷል; እግዚአብሔር ሥላሴ ነው ፤ ኢየሱስ ፍጹም አምላክ እና ፍጹም ሰው ነው። ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞች ናቸው። መጽደቅ በእምነት ብቻ ነው ፤ ክርስቲያኖች ቅዱስ መሆን አለባቸው; መጽሐፍ ቅዱስ የማይነቃነቅ የእግዚአብሔር ቃል ነው። እነዚህን ሁሉ ፅንሰ-ሀሳቦች ስንመለከት ፣ አንድ ሰው በጣም በደንብ የተማረ እና ሁሉንም ለመረዳት እንኳን መረጃ ሊኖረው እንደሚገባ ግልፅ ይሆናል ፣ ሁሉንም ያምናሉ።

አሁን በእርግጥ እኛ የዘረዘርናቸው ትምህርቶች አስፈላጊ የክርስትና ትምህርቶች ናቸው። ነገር ግን አንድ ሰው ስለእነዚህ አስተምህሮዎች ሳይሰማ እውነተኛውን የክርስትና እምነት እና የክርስትና ሥነ -መለኮት ሊኖረው እንደሚችል ግልፅ መሆን አለበት፡፡ መረዳቱ በጥልቀት ላይሆን እምነቱ ሁሉንም ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ የትኞቹ ትምህርቶች ለክርስትና እምነት በጣም አስፈላጊ ናቸው? የክርስትና ሥነ -መለኮት ለማለት ዝቅተኛው መለኪያ ምንድነው? በእውነቱ ፣ ያን ትክክለኛውን መስመር የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

የክርስትናን ሥነ -መለኮት ለመግለፅ ስንሞክር እነዚህ ዓይነት ችግሮች ያጋጥሙናል። ከአንዳንድ ሌሎች ሃይማኖቶች ጋር በተያያዘ እኛ እራሳችንን ለመለየት አስቸጋሪ አይደለም ፣ ግን አንድ ሥነ-መለኮት በትክክል ክርስቲያናዊ መሆኑን ለመለየት መሠረታዊ መለኪያዎቻችን ማግኘት በጣም ከባድ ነው፡፡

እነዚህ እና ሌሎች የክርስትና ሥነ -መለኮትን በመለየት ላይ ያሉ ችግሮች  በትምህርቶቻችን ውስጥ የሚኖሩንን ውይይቶች የሚመራ ትርጉም እናቀርባለን፡፡ ይህ ፍቺ ሊነሳ የሚችለውን እያንዳንዱን ጥያቄ አይመልስም ፣ ግን ጉልህ እና አጋዥ የሆነ ግልጽ መለኪያ ይሰጠናል። ይህ ፍጹም ፍቺ አይሆንም ፣ ግን ወደፊት ለመሄድ ያስችለናል፡፡

## አማራጭ ፍቺ

በእነዚህ ትምህርቶች ፣ የክርስቲያናዊ ሥነ-መለኮት ትርጓሜያችንን ወደ ዝነኛ እና ጥንታዊ የክርስትና የሐዋርያት የእምነት መግለጫ እናመራለን። ይህ የእምነት መግለጫ አሁን ባለው መልክ በ 200 ዓ.ም ገደማ የነበረ ሲሆን አሁን ባለው ሁኔታ የተቀረጸው በ700 ዓም አካባቢ ነበር፡፡ በመላው ዓለም የሚገኙ ክርስቲያኖች ይህንን የክርስትና እምነት መገለጫቸውን ለዘመናት ሲናገሩት ኖረዋል፡፡

*እኔ ሁሉን በሚችል፣*
*ሰማይና ምድር በፈጠረ በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ፡፡*
*በአንድ ልጁ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ፣*
*በመንፈስ ቅዱስ በተፀነሰው ፣*
*ከድንግል ማርያምም በተወለደ።*
*በጴንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን መከራን በተቀበለ ፣*
*በተሰቀለ ፣ በሞተ ፣ በተቀበረ።*
*ወደ ሲኦል ወረደ።*
*በሦስተኛው ቀን ከሙታን በተነሣ።*
*ወደ ሰማይ ዐረገ*
*እና ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ፣*
*ከዚያ በሕያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድ በሚመለስ አምናለሁ፡፡*

በመንፈስ ቅዱስ አምናለሁ ፣
ቅድስት አንዲት እውነተኛ ቤተክርስቲያን ፣
በቅዱሳን ኅብረት ፣
በኃጢአት ይቅርታ ፣
በሥጋ ትንሣኤ ፣
በዘላለም ሕይወት አምናለሁ። አሜን፡፡

ይህ ዓለም አቀፍ የክርስትና እምነት መግለጫ ክርስትናን በጣም ቀላል እና አስፈላጊ በሆኑ መንገዶች ያጠቃልላል። ይህ የክርስትና ሥነ -መለኮት መሠረታዊ ፍቺያችን ሆኖ ያገለግላል። ለእኛ ዓላማ ፣ ከዚህ የሃይማኖት መግለጫ ጋር የሚስማማ ሁሉም ሥነ-መለኮት እንደ ክርስቲያናዊ ሥነ -መለኮት ይቆጠራል።

> የክርስቲያናው ሥነ-መለኮት ፍቺ ለመስጠት በሐዋርያትን የእምነት መግለጫ ውስጥ ያሉትን ሐሳቦች መቀበል በጣም አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም እውነተኛ ክርስትናን “ክርስቲያን” ከሚባሉት ኑፋቄዎች እና ከሌሎች ሃይማኖቶች መለየት በጣም አስፈላጊ በመሆኑ ነው፡፡ ሆኖም ሁል ጊዜ የምንፈልገው ያህል ንፁህ እንዳልሆነ ሁል ጊዜ ማስታወስ አለብን። እኔ የምለው ፣ ለምሳሌ ፣ ኢየሱስ በጴንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን መሰቃየቱ ለክርስትና እምነት ወሳኝ ነው ለማለት የሚፈልግ አለ? አሁን ፣ አዎን ልንል እንፈልግ ይሆናል ፣ ኢየሱስ በእውነቱ በዚህች ምድር ላይ እንደኖረ ማመን አስፈላጊ ነውን ፣ ጴንጤናዊው ጲላጦስ ራሱስ? ምናልባት አስፈላጊ ላይሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ ፣ በአንዳንዱ ዝርዝር ላይ ጸጉር መሰንጠቅ ሊኖር ይችላል፡፡ በተጨማሪ ፣ አንዳንዶቻችን በእነዚያ የክርስትና እምነት መሠረታዊ ነገሮች ላይ ሌሎች ነገሮችን ማከል እንፈልጋለን። ለምሳሌ ፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ መጽሐፍ ቅዱስን አይጠቅስም። መጽሐፍ ቅዱስ የማይሻርና የማይሳሳት ወይም መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ የሚለውንና ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮችን አይጠቅስም።... ስለዚህ ፣ የሐዋርያትን የሃይማኖት መግለጫ እንደ መመዘኛችን ስለማድረጋችን ስናስብ ፣ የኦርቶዶክስ ክርስትና ምን እንደ ሆነ የሚያሳየውን ፍቺያችን ፣ አንዳንድ ውስንነቶች መኖራቸውን ማስታወስ አለብን፡፡ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ባለፉት መቶ ዘመናት ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያገናኘናል ፣ ዛሬም በዓለም ዙሪያ ከሚገኙ ከእውነተኛው የክርስቶስ አካል ጋር በሰፊው ያገናኘናል። ስለዚህ ፣ ክርስትናን ጠቅለል አድርጎ ከክርስቲያናዊ ኑፋቄዎችና ከሌሎች ሃይማኖቶች ለመለየት ኢጋዥ መንገድ ነው።
>
> — ዶ/ር ሪቻርድ ኤል ፕራት ፣ ጁኒየር

> የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ስለ ክርስቲያናዊ እምነት ያለን ግንዛቤ ማዕከል ነው። ክርስቲያን መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ዋና እምነቶችን ያንፀባርቃል። የተቀመጡ አሳቦች የተለያዩ መልዕክቶችን ያስተላልፋሉ፡፡ እኔ በብዙ መንገድ የኦርቶዶክሳዊነትን ድንበር ይገልጻል ብዬ አስባለሁ፡፡ አብ እና ወልድ እርስ በእርስ እንዴት እንደሚዛመዱ፣ ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት እንደምንገናኝ እና እግዚአብሔር ከፍጥረት ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ይናገራል። እነዚህ ሦስቱ አካላት የዚህን ሕይወት፣ የመዳንን፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ለመረዳት ማዕከል ናቸው.... ስለዚህ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ የሚጠቅመን ወሰኖችን ለማበጀት እና እያንዳንዱ ግንኙነት ከእግዚአብሔር ቃል አንጻር እንዲታይ ለማድረግ ነው፡፡
>
> — ዶ/ር ስኮት ማኑር




ለምሳሌ ፣ የሃይማኖት መግለጫው ፍጥረትን ይጠቅሳል። ሦስቱን የሥላሴ አካላት ማለትም አብን ፣ አንድ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን እና መንፈስ ቅዱስን ይጠቅሳል። እርሱም የሚያመለክተው ትስጉት ፣ ሞትን ፣ ትንሣኤን እና የኢየሱስን ዕርገት ነው። በተጨማሪም ስለ ኃጢአቶች ስርየት ፣ ስለ አጠቃላይ ትንሣኤ ፣ ስለ መጨረሻው ፍርድ እና ስለ ዘላለም ሕይወት ተስፋ ይናገራል። እንዲህ ዓይነቱን ጠንካራ እና ሰፊ መሠረት ስለሚሰጥ ፣ የሐዋርያትን የሃይማኖት መግለጫ እንደ የክርስቲያን ሥነ -መለኮት መሠረታዊ ፍቺያችን እንጠቀማለን። ምንም እንኳን ከዚህ አጭር ዝርዝር በላይ ስለሆኑት ትምህርቶች ብንናገርም ፣ ለዓላማችን ፣ አንድ ሥነ -መለኮት ከዚህ የሃይማኖት መግለጫ ጋር የሚስማማ ከሆነ ሥነ-መለኮቱ ክርስቲያናዊ እንደሆነ መናገር ይቻላል፡፡

ችግሮቻችንን በክርስትና ሥነ -መለኮት ትርጓሜዎች ለማሸነፍ ፣ እኛ እንደ መሠረታዊ ፍቺያችን የሐዋርያትን የሃይማኖት መግለጫ ጽሑፍ ተጠቅመናል። ይህን በማድረግ ፣ በክርስትና እምነት ሥነ -መለኮት ውስጥ ሁለቱም አንድነት እና ልዩነት እንዳሉ ወዲያውኑ ግልፅ ይሆናል።

## አንድነት በልዩነት

ተማሪዎች ሥነ -መለኮትን ማጥናት ሲጀምሩ፣ ስለ "ክርስቲያናዊ ሥነ -መለኮት" አንድ ነገር ብቻ እንደሆነ በልበ ሙሉነት ይናገራሉ። ነገር ግን ፣ ስለ ብዙ የተለያዩ አመለካከቶች የበለጠ ጠንቅቀው ሲያውቁ ፣ የሃይማኖት ሊቃውንት በዓመታት ውስጥ የተናገሩትን ሲረዱ ፣ ብዙውን ጊዜ "ክርስቲያናዊ ሥነ -መለኮቶች" ብሎ መጥራቱ የተሻለ እንደሆነ መናገር ይጀምራሉ፡፡ ቀደም ብለን እንደጠቀስነው ፣ በእውነተኛ ክርስትና ክልል ውስጥ እንኳን ፣ ታማኝ አማኞች ብዙ የተለያዩ አመለካከቶችን ይይዛሉ። ስለዚህ ፣ የትኛው ነው - የክርስትና ሥነ -መለኮት ወይስ ሥነ -መለኮቶች ነው ትክክል? አንድ ፣ የተዋሃደ የክርስትና ሥነ -መለኮት አለ? ወይስ ብዙ ፣ የተለያዩ የክርስትና ትምህርቶች አሉ? ዞሮ ዞሮ ሁለቱም ትክክለኛ መልስ ናቸው።

በክርስቲያኖች መካከል ብዙ የተለመዱ እምነቶች ፣ ልምምዶች እና ስሜቶች ስላሉ ስለ አንድ ነጠላ ፣ ስለተዋሃደ የክርስትና ሥነ -መለኮት ልንናገር እንችላለን። ነገር ግን እኛ እርስ በርሳቸው ስለሚለያዩ በርካታ የክርስትና ሥነ -መለኮቶች ለመናገር ዝግጁ መሆን አለብን። በመጀመሪያ በክርስቲያኖች መካከል ያለውን ሥነ -መለኮታዊ አንድነት እንመልከት።

## የተዋሃደ ሥነ -መለኮት

ሁሉንም የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናትን እና ቤተ እምነቶችን ስንመለከት ፣ በክርስቲያኖች መካከል ያለውን ሥነ -መለኮታዊ አንድነት ትርጉም ባለው መልኩ መናገር ከባድ ይመስላል። የማያምኑ ሰዎች ፣ “እናንተ ክርስቲያኖች ባመናችሁት ላይ እንኳን መስማማት አይትሉም። ክርስቲያን እንድንሆን ለምን ትጠብቃላችሁ? ” ብለው ሲነገሩ ስንት ጊዜ ሰምታችኋል? አንዳንድ ጊዜ የክርስቶስ ተከታዮች በማንኛውም ነገር ላይ መስማማት የማይችሉ መስሎ መታየቱን መቀበል አለብን። ግን መከፋፈል አንዱ ገጽታ ነው፡፡

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ እንዳስቀመጠው በዓለም ዙሪያ ያሉ እውነተኛ ክርስቲያኖች አንድ “ቅድስት ቤተክርስቲያን” አካል ናቸው። ምንም እንኳን ክፍፍሎች ቢኖሩም ፣ የክርስቶስ አካል የተዋሃደ ሥነ -መለኮት አለው፡፡ ምክንያቱም ክርስቲያኖች ከኑፋቄዎችና ከሌሎች የዓለም ሃይማኖቶች በሚለዩዋቸው በርካታ መሠረታዊ እምነቶች ላይ ይስማማሉ። በእነዚህ ትምህርቶች ውስጥ የክርስትናን ሥነ-መለኮት ስንመረምር ፣ ሁሉንም ክርስቲያኖች አንድ ላይ የሚቀላቀለውን የእምነት አንድነት አምነን መቀበል አለብን። ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን 4፡ 4-5 ላይ ስለ ቤተክርስቲያን አንድነት እንዲህ ብሎ ተናግሯል።

> በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤ አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት፤ (ኤፌሶን 4:4-5).

እንደ እውነቱ ከሆነ የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ አንድነት ሁሉም ክርስቲያኖች ያሏቸው ግብ መሆን አለበት። በዮሐንስ 17፡ 22-23 ላይ ኢየሱስ ራሱ ለዚህ ጸልዮአል።

> እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ፤ እኔም በእነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን፥ በአንድ ፍጹማን እንዲሆኑ፥ የሰጠኸኝን ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ፤ እንዲሁም ዓለም አንተ እንደ ላክኸኝ በወደድኸኝም መጠን እነርሱን እንደ ወደድሃቸው ያውቃል። (ዮሐንስ 17:22-23).

ቤተ ክርስቲያንን በቅርበት ስንመለከት ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው የተለያየ የሥነ-መለኮት አንድነት ደረጃ እንዳላቸው እናያለን። በሰፊው ትርጓሜ ፣ በእኛ ትርጓሜ መሠረት ፣ ሁሉም ክርስቲያኖች በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ በተገለፁት መሠረተ እምነት በማመን ሥነ -መለኮታዊ አንድነት አላቸው። የሃይማኖት መግለጫውን የሚያረጋግጡ ሁሉ የእምነት ባልንጀራቸው ስለሆነ የትኛውንም የቤተክርስቲያን ክፍል ቢከተሉ የሃይማኖት መግለጫውን ለሚደግፉ ሁሉ አክብሮት ፣ ትዕግሥትና ፍቅር እንድናሳይ ይህ መሠረታዊ አንድነት ይጋብዘናል። በዚህ ጉዳይ ላይ በኤፌሶን 4፡15 እንደተነገረን እውነትን በፍቅር መናገርን መማር አለብን።

በተጨማሪም ፣ በሃይማኖት መግለጫው ውስጥ ከተጠቀሱት በላይ የሆኑ እምነቶችን ስንጋራ በክርስቲያኖች መካከል ሥነ -መለኮታዊ አንድነት ይጨምራል። ለምሳሌ ፣ ኦርቶዶክስ ፣ ካቶሊኮች እና ፕሮቴስታንቶች እንደ ሥላሴ እና የክርስቶስ መለኮት ላይ ተመሳሳይ የእምነት አስተሳሰብ አላቸው። ነገር ግን ለመጀመሪያው እምነታቸው ታማኝ ሆነው የቆዩት የፕሮቴስታንት ቤተ እምነቶች ፕሮቴስታንት ካልሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ይልቅ እርስ በርሳቸው እጅግ ብዙ ሥነ-መለኮታዊ አንድነት አላቸው።

እኛ በጣም የጋራ ከሆኑት ጋር አንድነትን ለመፈለግ እና ከዚያ ብዙም የማይመሳሰሉንን እንደ ጠላት የመቁጠር አዝማሚያ ቢኖረንም ፣ ጌታችን ሁላችንንም ወደ አንድነት እንዲንመጣ ይመክረናል። በዚህ ምክንያት ፣ በክርስቲያኖች መካከል ያለው ልዩነት በክርስቶስ ካለን ሰፊ የጋራ መሠረት ላይ ትኩረታችንን እንዲያነሳ በፍጹም መፍቀድ የለብንም። ክርስቲያኖች በእያንዳንዱ ትምህርት ላይ መስማማት ስላልቻሉ ተስፋ ከመቁረጥ ይልቅ ፣ በአንድ ደረጃ ወይም በሌላ ፣ ክርስቲያኖች በእምነት ማዕከላዊ መርሆዎች ላይ መስማማታቸውን ማወቅ አለብን። ከዚህ አንፃር ፣ የክርስትና ሥነ -መለኮት የተዋሃደ እውነታ ነው። ከዚህ በበለጠ ፣ በክርስቶስ አካል ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የሚሄደውን ሥነ-መለኮታዊ አንድነት ማስተዋወቅ የእኛ ኃላፊነት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን 4፡13-16 እንዲህ በማለት አስቀምጧል፡-

> ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ። እንደ ስሕተት ሽንገላ ባለ ተንኮል በሰዎችም ማታለል ምክንያት በትምህርት ነፋስ ሁሉ እየተፍገመገምን ወዲያና ወዲህም እየተንሳፈፍን ሕፃናት መሆን ወደ ፊት አይገባንም፥ ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ፤ ከእርሱም የተነሣ አካል ሁሉ እያንዳንዱ

ክፍል በልክ እንደሚሠራ፥ በተሰጠለት በጅማት ሁሉ እየተጋጠመና እየተያያዘ፥ ራሱን በፍቅር ለማነጽ አካሉን ያሳድጋል።(ኤፌሶን 4:13-16).

እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን ያለው ፍላጎት እና እኛ እንድንከተለው የመሠረተው ግብ ሥነ -መለኮታዊ መከፋፈል አይደለም ፣ ነገር ግን በቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርቶች መሠረት ሥነ -መለኮታዊ አንድነትን ማሳደግ ነው።

*ይህ አስደሳች ነው። እኛ እንደ ክርስቲያኖች ከሚያጋጥሙን ፈታኝ ሁኔታዎች አንዱ "እኔና አብ አንድ እንደሆንን ቤተክርስቲያኔ ፣ ሕዝቤ ፣ አንድ እንድሆኑ እጸልያለሁ" የሚለውን የኢየሱስን ጸሎት በቁም ነገር መመልከት አለመቻላችን ነው። በዚያ ውስጥ ውጥረት አለ ፣ ምክንያቱም በአንድ በኩል ፣ "አስፈላጊው እውነት እንጂ አንድነት አይደለም" ብለን ወደ አንድ ጎን እንሳባለን፡፡ ሰዎች ያንን ሲያደርጉ ፣ ከእነርሱ ጋር ስለማይስማሙ ሌሎች ክርስቲያኖች ግድ የላቸውም። የአንድነት ጥሪ በእነርሱ እና በቤተክርስቲያኖቻቸው ላይ ምንም ዓይነት ተጽዕኖ የለውም። ነገር ግን ኢየሱስን፣ በልቡ ላይ እና በጸሎቱ ውስጥ ያለውን ነገር በቁምነገር የምንወስደው ከሆነ ፣ ከአንድነት ውጭ ሌላ አማራጭ የለንም፡፡ አንድነት በእውነት አስፈላጊ መሆን አለበት… እና መታገል ያለብን አንዱ ነገር ለእርስ በርሳችን እንዴት ዋጋ እንሰጥ? በሚለው ላይ ነው፡፡ አንድ ሳንሆን እንዴት አንድነትን እናሳያለን? እኔ ከሚታገልባቸው ነገሮች አንዱ አንድነትን ከተመሳሳይነት ጋር ማደባለቅ ይመስለኛል። አንድነት እና ተመሳሳይነት አንድ አይደለም። ስለዚህ አለመግባባቶች በመካከላችን ቢኖሩም አንድነት ሊኖረን ይችላል፡፡ በአንድ ጉዳይ ላይ ላንስማማ እንችላለን፡፡ ይህን አንድነት ከሚረዱ ነገሮች አንዱ «ከሌሎች ቤተ-እምነት የሆኑ ወንድሞችና እህቶች እኛ ያላየናቸውን ነገሮች ሊያሳዩን ይችላሉ» ብሎ ማሰብ ነው፡፡ ስለዚህ ልዩነትን በመፍቀድ እና በልዩነት ውስጥ ታማኝ ለመሆን በመሞከር አንድነትን መፈለግ እንችላለን።*

— ዶ/ር ኬሊ ኤም ካፒክ

ክርስቲያኖች በተለያየ ደረጃዎች አንድ ሲሆኑ ፣ በመካከላችን ያለውን የብዝሃነት ደረጃዎችን ማመንና መቀበል አስፈላጊ ነው። ከዚህ አንፃር ፣ እኛ ከአንድ ክርስቲያን ሥነ -መለኮት ይልቅ ፣ ስለ ብዙ የክርስትና ሥነ -መለኮቶች በትክክል እንናገራለን።

### *የሥነ-መለኮት ብዝኃነት*

ፕሮቴስታንቶች ማኅበራቸውን ከራሳቸው ውጭ ወደሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ሲያስተላልፉ ብዝኃነቱ እንደሚጨምር በቀላሉ ይገነዘባሉ። የተለያዩ ቤተ እምነቶች እርስ በእርስ ሲጋጩ ፣ ሁልጊዜ ማለት ይቻላል ብዝሃነትን ይጋፈጣሉ። ለምሳሌ የምስራቅ ኦርቶዶክስ እና ምዕራባዊያን አብያተ ክርስቲያናት አንድ ላይ ሲሰባሰቡ ልዩነቱ ጥልቅ ነው።

አሁን ፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለውን ብዝሃነት ስንጋፈጥ ፣ አንድ ከባድ ጥያቄ መጠየቅ አለብን - በመካከላችን ልዩነቶች ለምን ይኖራሉ? ሁላችንም አንድ መንፈስ አለን። ሁላችንም በአንድ ክርስቶስ እናምናለን። ሁላችንም ብዙ ማዕከላዊ እምነቶችን በጋራ እናጋራለን። ስለዚህ ፣ በክርስቲያኖች መካከል ብዝሃነትን የሚያመጣው ምንድነው? ይህንን ጉዳይ በሚመለከት ፣ በክርስትና ሥነ -መለኮት መካከል ቢያንስ ሁለት ዓይነት ልዩነቶችን ለመለየት ይረዳል።

ውስንነቶች። በመጀመሪያ ደረጃ ፣ አንዳንድ ልዩነቶች የሚኖሩት እያንዳንዱን ሥነ -መለኮታዊ እውነት በእኩል ኃይል ስለማንወክል ብቻ ነው። እኛ ሰዎች ስለሆንን አንዳንድ የክርስትና እምነት ገጽታዎችን ከሌሎች ገጽታዎች ይልቅ መርጠን ማጉላታችን የማይቀር ነው፤ ይህ የሰብዓዊነት ውስንነታችን አንዱ ነጸብራቅ ነው፡፡ እኛ በአንድ ጊዜ ለሁሉም ለእምነታችን ገጽታዎች እኩል ትኩረት መስጠት አንችልም። ይህ በሥነ -መለኮት ምሁራን እና በሥነ -መለኮት ላይ ያለው ውስነነት ብዙውን ጊዜ በክርስቲያኖች መካከል ያለውን የአስተምህሮ ልዩነት ይገልጻል፡፡ ይህ ዓይነቱ ብዝኃነት ከምርጫ እና ከአፅንዖት የሚመጣ ጤናማ እና በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች እንኳን በጻፉት እና አጽንዖት በሰጡት ነገር ልዩነት መኖሩ እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነቱን ብዝኃነት እንደሚደግፍ እናውቃለን።


ለምሳሌ ፣ እኛ አራት የተለያዩ ወንጌሎች አሉን ምክንያቱም እግዚአብሔር ማቲዎስን ፣ ማርቆስን ፣ ሉቃስን እና ዮሐንስን ስለ ኢየሱስ ሕይወት በተለያዩ የእውነት ገጽታዎች ላይ እንዲያተኩሩ አድርጓል። በማይሳነው የመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት የተመሩ ክርስቲያኖች በአፅንዖታቸው ስለተለዩ ፣ ዛሬ ለክርስቲያኖችም ተመሳሳይ በመሆኑ ልንደሰት ይገባናል። እግዚአብሔር የተለያዩ አበቦችን እና ዛፎችን እንደሚወድ ፣ በተራሮችም ሆነ በሸለቆዎች እንደሚደሰት ፣ እና የተለያዩ ሰዎችን በማፍራት እንደሚደሰት ፣ ልጆቹም በተለያዩ መንገዶች ሥነ -መለኮታቸውን ሲያሳድጉ ማየት ያስደስተዋል።

በክርስቶስ አማካኝነት ያለን አንድነት በሆነ መንገድ በአስተምህሮ ልዩነት ችግር ላይ ይወድቃል የሚለው አስተሳሰብ ትክክል አይመስለኝም። እኔ እንደማስበው ፣ በክርስቶስ ውስጥ ስፋት እና መለኪያዎች አሉ ፣ በክርስቶስ ማመን የተወሰኑ የጋራ እምነቶችን ያጠቃልላል ፣ እና ከዚህ ጋር የተወሰኑ ግንዛቤዎች ፣ የተወሰኑ ሀሳቦች ፣ አንዳንድ ትምህርቶች ከተገለጠልን የአዲስ ኪዳን መጽሐፎች አንጻር ከወሰኖቹ ውጭ ሊወድቁ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን የአዲስ ኪዳን ክርስቶስ ጠባብ አይደለም ፣ እና ከዚያ በእነዚህ ድንበሮች ውስጥ ቦታ አለ ፣ እነዚህ መለኪያዎች ፣ ለክርስትና እምነት ብዝኃነት ሥፍራ ይሰጣሉ፡፡ ትልልቅ የቤተ እምነቶችና የሥነመለኮት ወጎች ልዩነት ሊኖራቸው ይችላሉ፤ ሆኖም ቤተክርስቲያን ስለክርስቶስ መሠረታዊ የሆነው እምነት ትጠብቃለች፡፡

— ዶ/ር ዴቪድ አር ባወር

በገጠሪቷ አፍሪካ ውስጥ የክርስትና ሥነ -መለኮት በኒው ዮርክ ከተማ ካለው የክርስትና ሥነ -መለኮት ይልቅ የተለያዩ እውነቶችን እንዲመርጥ እና አፅንዖት እንደሚሰጥ መጠበቅ አለብን። የደቡብ አሜሪካ ክርስቲያናዊ ሥነ -መለኮት በቤጂንግ ካለው ክርስቲያናዊ ሥነ -መለኮት የተለየ እንደሚሆን መጠበቅ አለብን። ይህ ብዝሃነት ጌታ የተቤዣውን ሕዝቡን በራሱ ባህላዊ ቅንጅቶች መሠረት እና ለየራሳቸው ፍላጎቶች ምላሽ በመስጠት የእምነታቸውን የተለያዩ ገጽታዎች እንዲገልጹ በመምራቱ የመጣ ነው፡፡

*ኃጢአትና ስህተት.* በሁለተኛ ደረጃ ፣ ሌሎች የብዝሃነት ዓይነቶች በጣም ንፁህ አይደሉም እና የበለጠ ጥንቃቄ ይፈልጋሉ። እነዚህ በኃጢአተኝነት እና በስህተት የሚመሩ ልዩነቶች ናቸው። የማጉላት ወይም የመምረጥ ጉዳዮች ከመሆን ይልቅ እነዚህ ልዩነቶች የሚመጡት ቡድኖች ወይም ሰዎች ወደ ሐሰተኛ ትምህርቶች ፣ ልምዶች እና ስሜቶች ውስጥ ሲገቡ ነው።




የተለያዩ ክርስቲያኖች በተፈጥሮ ለተለያዩ አስተምህሮዎች አጽንዖት ይሰጣሉ፡፡.

ስለዚህ ፣ እኛ እንደ ክርስቲያኖች ይህ በእውነት አስደሳች እንቆቅልሽ አለን ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር የሥልጣን ቃል ነው ብለን ስለምናምን ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እምነታችንን ፣ ሕይወታችንን ፣ ለእርሱ ያለንን ቁርጠኝነት - በማህበረሰብ ውስጥ የምንኖርበት መንገድ ፣ ስለወንጌል የምንናገርበት መንገድ ፣ እኛ ለሌሎች ሰዎች የምንቀርብበት መንገድ እንደሚገዛን እናምናለን፡፡ ሆኖም ቅዱሳት መጻሕፍት የሚያስተምሩት ሁል ጊዜ ለሁሉም ግልፅ አይደለም። ስለሆነም እኛ በሚያስተምረን ነገር ለመከተል እና ለመገዛት እንፈልጋለን ፣ ግን እኛ ሁል ጊዜ ትክክል አይደለንም፡፡ መጽሐፉ የሚያስተምረው እኛ ያሰብነው

እንደሆነ እናስባለን፡፡ እኛ በአንድ ነጥብ ላይ እንደተሳሳትን ካወቅን፣ ያንን ማሰብ ትተን ትክክለኛውን ማሰብ እንጀምራለን፡፡ እኔ በጣም ጠቃሚ ምክር ወይም ይህን አሳብ ለማስተናገድ በጣም አጋዥ መንገድ እንደሆነ የማስበው “ሥነ -መለኮታዊ ትሕትና” ብለን የምንጠራው ይመስለኛል። ይህ ማለት የጉድለቶቻችንና ውድቀቶቻችን ግንዛቤ እንዳለን መረዳት ነው፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት የሚሉትን ካወቅን እኛ በአስተሳሰባችን ልንሳሳት እንደምንችል እንገነዘባለን፡፡ “በዚህ ላይ ስህተት ልሠራ እችላለሁ” የሚለው አባባል ፣ እኛ ለእዚህ ቁርጠኝነት ካለን እና በቅዱሳት መጻሕፍት መልእክት ስናምን ፣ መልዕክቱ እኛ ላይ ሥልጣን እንዲኖረ እንፈቅዳለን። “እኔ በዚህ ላይ ተሳስቻለሁ” የሚለው አስተሳሰብ ለመማር እንድንነሳሳ ሊያደርገን ይገባል። ከእኛ አሳብ ጋር የማይስማሙ ሌሎች ሰዎችን ለማዳመጥ እንድንነሳሳ ሊያደርገን ይገባል። ስለሆነም ከመፍራት አልፎ ተርፎም ከመናደድ ይልቅ ፣ “ ይህ ቅዱሳት መጻሕፍት የሚሉት አይደለም” የሚለው ሌሎች ትርጓሜዎችን ለማዳመጥ ፍላጎት እንዲኖረን በአስፈላጊነቱን እንዲናምን ያግዘናል፡፡ ምክንያቱም እኛ ተሳስተን ሊሆን ይችላል፤ እነርሱ ተሳስተው ሊሆን ይችላል፡፡ እርስ በእርስ በመደማመጥ ወደ ትክክለኛው አሳብ ትንሽ ልንቀርብ እንችላለን፡፡

— ዶ/ ቲም ሳንስበሪ

ስህተትን ለመለየት ፣ በአንድ በኩል ራስን መመርመር አስፈላጊ ነው፣ ወደ ሥነ-መለኮታችን የገባውን ማንኛውንም የሐሰት እምነትን ለመተው ዝግጁ መሆን አለብን። በሌላ በኩል ደግሞ ሌሎች አማኞችም ግንዛቤያቸውን እንዲያሻሽሉ ለመርዳት ዝግጁ መሆን አለብን። አንዳንድ ጊዜ ይህ በጣም ቀላል ይሆናል ፣ ግን ሌላ ጊዜ ይህ ሂደት በጣም ከባድ ይሆናል። እናም በዚህ እርግጠኛ መሆን እንችላለን -ክርስቶስ በክብር እስኪመለስ ድረስ ራሳችንንም ሆነ ሌሎችን ከስህተቶች ፈጽሞ ማጽዳት አንችችም፡፡ ሆኖም እንደ የክርስቶስ ተከታዮች የእኛ ኃላፊነት ራሳችን ለቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርቶች እውነተኛ ሆነን ሌሎችንም እንዲሁ እንዲያደርጉ ለመርዳት ጠንክረን መሥራት ነው። ጳውሎስ በ 1 ጢሞቴዎስ 4:16 ላይ የጻፈውን አስታውሱ።



ሁልጊዜ ለቅዱሳት መጽሓፍት ትምህርቶች እውነተኞች ሆነን መገኘት አለብን

> ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ፥ በእነዚህም ጽና፤ ይህን ብታደርግ፥ ራስህንም የሚሰሙህንም ታድናለህና።(1 ጢሞቴዎስ 4:16).

በአገልግሎታችን በምናደርገው ሥራ ውስጥ ከተለያዩ የእምነት ዳራ፣ ከተለያዩ የእምነት ወጎች የተውጣጡ የተለያዩ ሚስዮናውያን ያጋጥሙናል ፣ ከእነርሱ ጋር አብረን መስራታችን አስፈላጊ ይመስለኛል። በወንጌላውያን ማኅበረሰብ ውስጥ ብዙ የሚያመሳስለን ነገር አለ። እኛ የማንስማማባቸውም ጉዳዮች አሉን። በፍጻሜ ጊዜያት እና በጥምቀት እና በመንፈሳዊ ስጦታዎች ላይ ሁል ጊዜ መከፋፈል ይኖራል፡፡ እነዚህ ነገሮች አብያተ ክርስቲያናት የሚለያዩባቸው ሦስት ነጥቦች ናቸው፡፡ ግን ብዙ የሚያመሳስለን ነገር አለ። እኔ የነገረ መለኮት ምሁራኖቻችን እና ፓስተሮቻችን በቅድሚያ ሊያሳስባቸው የሚገባው እኛ ሁላችንም ለምንስባባቸው ነገሮች እውቅና መስጠት ይመስለኛል። ያንን ባደረግን ቁጥር በእነዚያ መሠረታዊ የእምነት ነጥቦች ላይ የአንድነት እና የጋራነት ስሜትን እንዳብራለን፡፡ ከዚያም በምንለያይባቸው ጉዳዮች ላይ አንዱ ሌላውን ከመኮነን ይልቅ በጸጋ ለመነጋገር ዕድል ይኖረናል፡፡

— ዶ/ር ስቲቭ ኩርቲስ

በእነዚህ ትምህርቶች ውስጥ ‹የክርስትና ሥነ -መለኮት› በሚለው ቃል ምን ማለት እንደሆነ አይተናል ፣ አሁን ሁለተኛው ርዕሳችን ማለትም ክርስቲያናዊ ወጎች አብረን እንመልከት፡፡

# ክርስቲያናዊ ትውፊቶች

ለፕሮቴስታንቶች የክርስትናን ትውፊቶች መጠራጠር ተፈጥሯዊ ነው። እኛ በተሐድሶው ውስጥ ሥር የሰደድን እንደሆንን እናስባለን፤ የፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ አራማጆች ከሁሉም የሰው ወንች ይልቅ ለቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን የበላይነት ቅድሚያ ይሰጣሉ፡፡ ያም ሆኖ ሁሉም የሰው ልጅ ወንች ከቅዱሳን መጻሕፍት ጋር ይጋጫሉ ማለት አይደለም። ወደፊት እንደምንመለከተው ቅዱሳት መጻሕፍት እራሳቸው የክርስትና ወንች መንፈስ ቅዱስ ለቤተክርስቲያን የሰጠውን ጥበብ እንደሚገልጹ ስለሚያስተምር በውስጣቸው ብዙ ዋጋ አለ፡፡ ስለዚህ የክርስትናን ሥነ-መለኮት ስንገነባ ሥነ-መለኮታዊ ወንች የሚኖራቸው ሥፍራ ምንድነው?

ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ሦስት ርዕሶችን እናነሳለን፡፡ በመጀመሪያ "ሥነ -መለኮታዊ ወግ" የሚለውን ቃል እንገልፃለን። ሁለተኛ የአንዳንድ ሥነ -መለኮታዊ ወንችን ዝንባሌዎች እንመረምራለን። ሦስተኛ በሕይወታችን ውስጥ የሥነ -መለኮታዊ ወንችን አስፈላጊነት እንመረምራለን። ስለ ክርስቲያናዊ ሥነ -መለኮታዊ ወግ ስንናገር በመጀመሪያ ምን ማለታችን እንደሆነ እንመልከት።

## የክርስቲያናዊ ትውፊት ትርጓሜ

የወንጌላውያን ክርስቲያኖች "ወግ" የሚለውን ቃል በብዙ መንገዶች ይጠቀማሉ፤ ስለዚህ እኛ እዚህ እንዴት እንደምንጠቀም መግለፅ አለብን። እኛ አሉታዊ ትርጓሜ በማቅረብ ጉዳዩን በመጀመሪያ እናብራራለን - ምን ማለታችን እንዳልሆነ በማብራራት - ከዚያም አዎንታዊ ትርጓሜ በመስጠት - ምን ማለታችን እንደሆነ እንገልጻለን። በመጀመሪያ ፣ ዛሬ በብዙ የወንጌላውያን ቡድኖች ውስጥ "ትውፊት" የሚለው ቃል በጣም አሉታዊ ትርጓሜዎች አሉት፤ ምክንያቱም "ባህላዊ" ብለን ከምንጠራው ጋር በቅርበት የተቆራኘ ስለሆነ ነው።

### አሉታዊ ትርጓሜ

የአሜሪካው የሥነመለኮት ሊቅ ጆን ፍሬም እንዳስቀመጠው -

**«ባሕላዊነት» የሚኖረው መጽሐፍ ቅዱስ በብቻ የሚለው አሳብ ሲጣስ ነው፡፡**

በሌላ አነጋገር ፣ ትውፊታዊነት ሥነ -መለኮታዊ እምነቶችን በሰው ምርጫዎች ላይ ይመሠርታል ፣ በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ሳይሆን በተለመዱ ባህላዊ ምርጫዎች ላይ ያተኩራሉ፡፡ በማርቆስ 7፡8-13 ላይ ኢየሱስ እነዚህን ቃላት ለጻፎች ፣ ለፈሪሳውያን እና ለሰዱቃውያን ተጠቅሞበታል-

> የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትታችሁ ....የሰውን ወግ ትጠብቃላችሁ...ወጋችሁን ትጠብቁ ዘንድ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እጅግ ንቃችኋል። (ማርቆስ 7:8-13).

የክርስቶስ ተከታዮች ባህላዊነት/ወግ ተከታይነትን ውድቅ ማድረግ አለባቸው ምክንያቱም ይህን መቀበል የቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን የሆነው ነገር ለሰብአዊ አስተያየት ሥፍራ መስጠት ይሆናል፡፡ መለኮታዊ መገለጥ ሳይሆን የሰዎች ምኞት እምነታችንን በቀላሉ ሊመራ ስለሚችል ፣ ኢየሱስ በዘመኑ እንዳደረገው ሁሉ ባህላዊነትን በሁሉም መልኩ መቃወም አለብን።

> *በመጀመሪያ ፣ ለክርስቲያኖች ወግ ጥሩ ገጽታ እንደሆነ አስባለሁ፡፡ የእኛን አስተምህሮዎች ጠቅለል ባለ ሁኔታ የምናገኝበት ነው። ነገር ግን ከወግ ጋር ተያይዘው ስለሚመጡ አደጋዎችም መጠንቀቅ አለብን። አንዳንዶቻችን ኢየሱስ የሰውን ወግ በመታዘዝ የእግዚአብሔርን እውነት ችላ ያሉትን ፈሪሳውያንን እና የሕግ መምህራንን የገሰጸበትን የማርቆስ 7 ን እናውቃለን፡፡ ወደ አእምሮዬ ከሚመጡ ታሪኮች አንዱ እኔ የጎበኘኋት አንዲት ቤተ ክርስቲያን ናት። ይህች ቤተክርስቲያን በጣም መደበኛ እና በጠዋት የጸሎት መጽሐፍትን ማንበብ ትወድ ነበር። ወደዚህች ቤተክርስቲያን የሚመጡ የዩንቨርሲቲ ወጣት ተማሪዎች ነበሩ፤ በዕድሜ ገፋ ሰዎች እነዚህን ወጣቶች አልወደዱአቸው ምክንያቱም ወጣቶቹ ወገኖችን አያከብሩም ብለው ስላሰቡ ነበር፡፡ የጠፉና ጌታን የሚሹ ወገኖች እንደሆኑ አስበው ወደ እነርሱ መሄድ ሲገባቸው፣ ጌታን ፈልገው ወደ እነርሱ የመጡ ወጣቶች ወደ ቤተክርስቲያናቸው እንዳይመጡ አገዱአቸው፡፡ ይህ ወግ ለወንጌል እንቅፋት ከሚሆንባቸው መንገዶች አንዱ ነው፡፡*

— ዶ/ር ሲንዶ ደስ ይበልህ

በሁለተኛ ደረጃ፣ «ባሕላዊነት» አሉታዊ ትርጉሟ ቢኖረውም «ትውፊትን» በሌላ እይታ መመልከት እንችላለን፡፡ በዚህ ዘመን ላሉ ወንጌላውያን ጆሮ እንግዳ በሚመስል መንገድ ሐዋርያው ጳውሎስ ትውፊት በክርስቶስ አካል ውስጥ የሚኖረውን አዎንታዊ ሚና ተናግሯል፡፡

## አዎንታዊ ትርጓሜ

ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ቆሮንቶስ 15፡3 ላይ የጻፈውን መልዕክት አስተውሉ፡-

እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ እንዲህ ብዬ። መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፥ ተቀበረም፥ (1 ቆሮንቶስ 15:3).

በግሪክ "ሰጠኋችሁ" የሚለው አገላለጽ ፓራዲዶሜ (παραδίδωμι) እና "የተቀበልሁትን" ፓራላምባኖ (παραλαμβάνω) ማለት ነው። እነዚህ ቃላት በጳውሎስ ጽሑፎች ውስጥ የክርስትና ትምህርቶችን ማስተላለፉን ለመግለጽ ብዙ ጊዜ ተጠቅሰዋል። ይህ እውነታ ለውይይታችን አስፈላጊ ነው ምክንያቱም እነዚህ ቃላት በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የአይሁድ ወገኖች የአይሁድን ወግ ትምህርቶች ለመግለጽ በጥቅም ላይ የዋሉ ቃላት ነበሩ

በእውነቱ ፣ ጳውሎስ የክርስትናን እምነት ከሰው ወደ ሰው ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ወግ አድርጎ ተመልክቷል። ምንም እንኳን "ወግ" የሚለውን ቃል ከጳውሎስ አጠቃቀም ትንሽ ለየት ባለ መንገድ ብንጠቀምም ፣ "የክርስትና ወግ" ወይም "የክርስትና ትዉፊተ" የሚሉትነ ቃላት መጠቀም መተው የለብንም። በግልጽ ለማየት እንደሚቻለው ፣ ጳውሎስ ራሱ የትውፊት ቋንቋን በአዎንታዊ መልኩ ተጠቅሞበታል።

ቅዱሳት መጻሕፍት ራሱ በቃልም ሆነ በጽሑፍ ስለሚተላለፈው ሐዋርያዊ ወግ በአዎንታዊነት ይናገራሉ። እንደ ወንጌላውያን ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማስተላለፍ እንፈልጋለን ስንል ፣ ሐዋርያዊ ወግን መጠበቅ እንፈልጋለን ማለታችን ነው… የተሐድሶ አራማጆች በቅዱሳት መጻሕፍት እይታ የቤተክርስቲያንን ትውፊት በሚመዝኑበት ጊዜ ከቅዱሳት መጻሕፍት የማይስማሙትን ለመተው ነጻ ነበሩ፡፡ ነገር ግን የቤተክርስቲያን ትውፊት ከሐዋርያት ወግ ጋር በሚስማማበት ጊዜ - በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እንደተጠቀሰው- የተሐድሶ አራማጆች እነዚያን ወጎች ጠብቀዋል፡፡

— ዶ/ር አንድሪው ፓርሊ

ባህሎቻችን ብዙ ጥቅሞች አሉ፣ አንዳንድ ጊዜ የአምልኮ ሥርዓቶች ብለን እንጠራለን። ሰዎች ማን እንደሆኑ ማስታወስ ፣ እግዚአብሔር ማን እንደሆነ እና እግዚአብሔር የሠራውን ዘወትር ለማስታወስ ፣ እና ብዙ ወጎች እና የአምልኮ ሥርዓቶች ለማስታወስ ይረዱናል። ያንን ቦታ ለባህሎች እና ለአምልኮ ሥርዓቶች ሲሰጡ እና እግዚአብሔር ማን እንደ ሆነ ፣ እግዚአብሔር ምን እንደሠራ ፣ የሰው ልጅ ማን እንደሆነ እና የሰው ልጅ አቋም ምን እንደሆነ ለማስታወስ ሲጠቀሙበት ፣ በእግዚአብሔር ላይ ያለንን እምነት ለማጠንከር ይረዳናል። የእግዚአብሔርን ቦታ ፈጽሞ መውሰድ የለባቸውም ፤ የኢየሱስን ቦታ እና የእርሱን ብቃቶች በጭራሽ መውሰድ የለባቸውም። እነርሱ ማሳሰቢያ ብቻ ናቸው። እነርሱ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ምን ማለት እንደሆነ እና እንዴት እንደምናዳብር ፣ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያለውን ግንኙነት እንድንፈቅድ እንዴት እንደፈቀደ እና እነዚያ ሥርዓቶች እና ወጎች እርሱን እንድናስታውሰው ይረዱናል።

— ቀሲስ ፓብሎ ቶረስ ፣ ትርጉም

ለዓላማችን ፣ ሥነ -መለኮታዊ ወግን እንደሚከተለው እንገልፃለን-

በአንጻራዊነት ለረጅም ጊዜ የቆየ አብያተ ክርስቲያናትን ከእርስ በርስ የሚለይ ሥነ -መለኮታዊ ዶክትሪን ፣ ልምምድ ወይም ስሜት ነው፡፡

ይህንን ፍቺ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች እንክፈለው። በመጀመሪያ ፣ ትውፊት "በአንጻራዊ ሁኔታ ለረጅም ጊዜ የቆየ ዶክትሪን ፣ ልምምድ ወይም ስሜት" ነው። ያም ማለት በእነዚህ ትምህርቶች ውስጥ ስለ ሥነ -መለኮታዊ ትውፊት ስንናገር ፣ በቅርቡ የተጀመረ አንድ ነገር ማለታችን አይደለም። ይልቁንም ፣ የእምነት ስርዓት ሥነ -መለኮታዊ ወግ የሚሆነው ለተወሰነ ጊዜ ሲኖር ብቻ ነው። በእኛ ትርጓሜ መሠረት ፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ ለዓመታት ተቀባይነት ያገኙ እምነቶች ብቻ እንደ ወጎች ለመቆጠር ብቃትን ያገኛሉ፡፡


ሁለተኛ ፣ ሥነ -መለኮታዊ ወግ "የቤተክርስቲያንን ቅርንጫፎች እርስ በእርስ ይለያል"። በሌላ አነጋገር ፣ ስለ ስለአንዳንድ ቤተ-እምነቶች ወይም የአማኞች ህብረቶች ልዩ መለያዎች በአእምሮአችን ይዘናል፡፡ መጥመቃውያንን መጥመቃውያን የሚያደርገው ምንድን ነው? የመጥመቃውያን ወግ ነው። ሜቶዲስት ሜቶዲስት የሚያደርገው ምንድን ነው? የሜቶዲስት ወግ ነው። የአማኞች ቡድኖች ለረዥም ጊዜ የጋራ አመለካከቶችን ካላቸው፣ እነዚህ አመለካከቶች የተለዩ ሥነ -መለኮታዊ ዱካዎቻቸው ይሆናሉ። ከአንድ ቤተ-እምነት ጋር የበለጠ ወዳጅነት ይሰማቸዋል፡፡

> ክርስቲያናዊ ወጎች ወይም ቤተ-እምነቶች ቅርንጫፎች እንዲሁም የተለያዩ ቤተ-እምነቶች አጽንዖት የሚሰጧቸውን የተለያዩ ነገሮች እና ባለፉት ዓመታት የተከተሏቸውን መንገዶች በተመለከተ ፣ ወደ ጽንፍ መሄድ ቀላል ነው። አንድ ጽንፍ በሕይወታችሁ ላይ ማንኛውንም ዓይነት ተጽዕኖ አለመቀበል ነው - እናንተ በግል ሕይወታችሁ፣ በግለሰብ ከክርስቶስ ጋር መራመድን እና መጽሐፍ ቅዱስን በግለሰብ ደረጃ ለማንበብ አፅንዖት ትሰጣላችሁ። ይህንን ከመጠን በላይ የሚያጉሉ ሰዎች መጨረሻቸው እንደ ቤት አልባ ሰው ይሆናሉ። ምናልባት በመንገድ ላይ የሚሄድ ቤት የሌለውን ሰው አይታችሁ ከሆነ ይህንን ታስተውላላችሁ፣ ያ ሰወ አንድን ነገር አንስቶ በኪረጢቱ ውስጥ ወይም በጋሪው ውስጥ ያስቀምጠዋል፣ እና ይሄዳል፤ ከዚያም አንድ ሌላ ነገር በመንገድ ላይ እንደቀረ ያስተውላል። ቦርሳው በእውነቱ ባልተጣጣሙ ነገሮች ብቻ ተሞልቷል ፣ ሕይወቱ የተበታተነ ነው። አንድነት የለውም። የሚሄድበት ቤት የለውም። ስለዚህ ያ አንድ ጽንፍ ነው ፣ ያ ከፍ ያለ ግለሰባዊነት፣ የክርስትናን ወጎች ወይም ቤተ-እምነቶቹንና ጥበባቸውን አለመቀበል ነው፡፡
>
> ሌላኛው ጽንፍ ትውፊትን ፣ ቤተ-እምነትን፣ የተለያዩ የቤተክርስቲያን ክፍሎች ለዓመታት የተከተሉትን ዱካ እንደ እስር ቤት መውሰድ ነው፡፡ ከትውልድ ወደ ትውልድ የተላለፈ እና ምንም መስኮቶች የሌሉበት ህንፃ ውስጥ እንዳለ ሰው ራስን በእነርሱ ውስጥ መቆለፍ ትችላላችሁ፣ ለመውጣት በር የለም። ለምን ይህን ታደርጋለህ? ለምን እንዲህ ታምናለህ? ለምን እንደዚህ ይሰማሃል? "ቤተክርስቲያኔ እንዳምን፣ እንዳደርግና እንዲሰማኝ ስለምትነግረኝ ነው፡፡» ያ የክርስትናን ተውፊት ልክ እንደ እስር ቤት ማድረግ ነው፡፡ እናንተ ቤት እንደሌለው ግለሰብ ያለ ክርስቲያናዊ ትውፊት እንዲትሆኑ አንፈልግም እንዲሁም የአንድ ቤተ-እምነት እስረኛ እንድትሆኑም አንፈልግም፡፡ ምክንያቱም እናንተ አባል ከሆናችሁት ቤተ-እምነት ውጭ ካሉ ቤተ-እምነቶች ብዙ መማር ትችላላችሁ፡፡
>
> እኔ ብዙውን ጊዜ ስለ አንድ ቤተ እምነት ወይም የቤተክርስቲያን ቅርንጫፍ ወይም ለዓመታት የተከተሏቸውን መንገዶች - ወግ ፣ የክርስትና ወግን - እንደ ቤት አስባለሁ። አሁን ፣ ቤት ምን እንደሚመስል ታውቃላችሁ። የምትተኙበት ቦታ ነው። የምትሄዱበት እና ምቾት የሚሰማችሁ ቦታ ነው። እናንተ የምትገኙበት ቦታ ነው፡፡ ሌሎች ሰዎች ከሚያደርጉት ሊለዩ በሚችሉ መንገዶች በቤታችሁ ውስጥ አንዳንድ ነገሮችን ታደርጋላችሁ። ምክንያቱም ቤታችሁ ነው፡፡ እኔ ስለ ቤተ-እምነት፣ ስለሚሰጡን ህጎች፣ ስለሚሰጡን ፖሊሲዎች፣ ስለ ዶክትሪን ማጠቃለያዎቻቸው እና እንዲሰማን የሚነግሩንን መንገዶች ማሰብ በጣም ጠቃሚ ይመስለኛል። ያንን እንደ ቤታችን እንያዘው፡፡ በሕይወታችን ውስጥ ያሉትን ክፍተቶች ለመሙላት፣ በክርስቶስ አካል ላይ ብዙ መታመን እና እግዚአብሔርን በሚያስደስት መንገድ ለመኖር ነገሮችን በጥንቃቄ ማሰብ ይኖርብናል፡፡ ግን በተመሳሳይ ጊዜ ከቤተ-እምነታችን ውጭ - ወጋችን - ጓደኞችን ማፍራት ፣ ከእነርሱ መማር እና ወደ ቤተ እምነታችን - ወደ ራሳችን ቤት መመለስ እና ነገሮችን ከመጽሐፍ ቅዱስ እይታ ለመለወጥ መሥራት አለብን፡፡
>
> — ዶ/ር ሪቻርድ ኤል ፕራት ፣ ጁኒየር

አሁን በክርስትና ሥነ-መለኮታዊ ወጎች ምን ማለታችን እንደሆነ ከገለፅን፣ አንዳንድ የስነ-መለኮታዊ ወጎች ዝንባሌዎችን ማስተዋል አለብን።

## የትውፊት ዝንባሌዎች

ብዙ ቤተ-እምነቶች በሥነ-መለኮታዊ ዝንባሌዎች የተለዩ መሆናቸውን ሁላችንም እንገነዘባለን። ብዙ የክርስቶስ ተከታዮች በግልፅ እና በአእምሮአቸው ውስጥ ወደ አንድ የሥነ-መለኮታዊ ወግ ራሳቸውን ይመድባሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ እንዲህ አያደርጉም፡፡ እኛ ብናውቀውም ባናውቀውም፣ ሁላችንም በሥነ -መለኮታዊ ወጎቻችን በጥልቅ ተነክተናል። እነዚህ ሥነ-መለኮታዊ ዝንባሌዎች እኛ ባነበብናቸው መጻሕፍት፣ በምንሰማቸው ስብከቶች፣ በምንገኝባቸው አብያተ ክርስቲያናት እና በያዝናቸው ክርስቲያን ወዳጆች ይወከላሉ። እነዚህ ወጎች ከመጠን በላይ በእኛ ላይ ተጽዕኖ እንዳያሳድሩ ተስፋ ካደረግን ፣ ስለ እነዚህ ተጽዕኖዎች እና ጥንካሬዎቻቸው እና ድክመቶቻቸው ማወቅ አለብን።




በቀደመው ትምህርት፣ ሥነ-መለኮት ኦርቶዶክስን (ትክክለኛ ወይም እውነተኛ ትምህርቶችን) ፣ ኦርቶፕራክሲስን (ትክክለኛ ተግባር ወይም ልምምድ)፣ እና ኦርቶፓቶስን (ትክክለኛ ስሜቶችን ወይም ፍልቀ-ስሜቶችን) የሚያካትት መሆኑን አስተውለናል። በዚህ ምክንያት፣ በክርስትና ውስጥ የተለያዩ ሥነ-መለኮታዊ ወጎች ከእነዚህ ሦስት ምድቦች በአንዱ ወይም ምናልባትም በሁለት ውስጥ እንደሚወድቁ ማስተዋል ጠቃሚ ነው።

አንዳንድ ሥነ-መለኮታዊ ወጎች ኦርቶዶክስን የማጉላት ዝንባሌ አላቸው፣ አንዳንዶቹ ወደ ኦርቶፕራክሲስ እንዲሁም አንዳንዶች ደግሞ ኦርቶፓቶስን ያጎላሉ። በመጀመሪያ፣ አንዳንድ በኦርቶዶክስ ላይ አፅንዖት የሚሰጡ ቤተ-እምነቶች ከሌሎች እንዴት እንደሚለዩ እንመልከት።

## ኦርቶዶክሳዊነት

ማንነታቸውን በዋናነት ከያዙት አስተምህሮዎች አንፃር የሚመለከቱ ቤተ-እምነቶች እንዳሉ ሁላችንም እናውቃለን። የማስተማር አገልግሎቶቻቸው እና የአስተምህሮ አቋሞቻቸው የክርስትና እምነታቸውን እምብርት ነው፡፡ እንደ አለመታደል ሆኖ እነዚህ ቤተ-እምነቶች በአስተምህሮ ላይ የሚጨቃጨቁ ናቸው፡፡ ያም ማለት በአስተምህሮ ውዝግቦች ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ተጠምደው ይገኛሉ፡፡ ብዙውን ጊዜ ለአስተምህሮ ወጥነት አጥብቀው ይከራከራሉ። ይህ በአስተምህሮዎች መጨናነቅ ብዙውን ጊዜ ወደ አእምሯዊነት ይመራል፣ ይህም የእምነትን መረጃ መማር እና መረዳት በራሱ የመጨረሻ ግብ ይሆናል።





በአስተምህሮ ላይ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት ተግባራችንናa ስሜቶቻችንን ችላ እንድንል ያደርገናል

> *የቅዱሳት መጻሕፍትን አስተምህሮ ወይም ጽንሰ -ሀሳቦች ስናጎላ ፣ ሰዎች "ምሁራዊነት" ከሚሉት መራቅ እንፈልጋለን። ነገር ግን ያ አእምሮን ከማስቀረት ወይም አእምሮን ከማራቅ ጋር አንድ አይደለም... ጳውሎስ የሚናገረው መንፈስ ከመንፈሳችን ጋር በአንድነት መመስከሩ ብቻ አይደለም ፣ ነገር ግን ስለ መንፈስ አእምሮ ይናገራል። በተጨማሪም ስለ አእምሮ መታደስ ይናገራል፣ አዕምሮ አስፈላጊ ሚና ይጫወታል። አእምሮ የማንነታችን አካል ነው፣ እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠን ስጦታ ነው፡፡ ስለዚህ ወደ ቅዱሳት መጻሕፍት ስንቀርብ ያንን ልንጠቀምበት እንችላለን... ግን "እኔ አዋቂ ነኝ ፣ ሌላውን ሁሉ ዝቅ አድርጌ ማየት እችላለሁ" የሚል አእምሮ ዐይነት አይደለም። ስብከትን እየሰማን እና ከዐውደ-ጽሑፍ ውጭ አንድ መጽሐፍ ቅዱስ ስንሰማ፣ "አሃ ፣ ከእነርሱ የበለጠ ብልህ ነኝ" የሚልም አእምሮም አይደለም፡፡ ወጣት ክርስቲያን በነበርኩበት ጊዜ እንዲህ ዐይነት ፈተና ነበረብኝ። ምክንያቱም አንዳንድ ጊዜ እዚያ የሚነገር ዋጋ ያለው ነገር አለ ፣ ትሁት የሆነ አእምሮ ሊኖረን ይገባል ፣ እግዚአብሔር ሊያስተምረን ያለውን ለመማር ፈቃደኛ የሆነ አእምሮ ያስፈልገናል፡፡ ያንን አእምሮ ለአገልግሎት እንጠቀማለን።*
>
> *— ዶ/ር ክሬግ ኤስ ኬነር*

ሁለተኛ ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ሌሎች ትውፊቶች ኦርቶዶክሳዊነትን ከማጉላት ይልቅ ፣ በኦርቶፕራክሲያቸው የበለጠ ራሳቸውን የመለየት አዝማሚያ አላቸው።

## ኦርቶፕራክሲስ


ከሚያስተምሩት በተቃራኒ በሚያደርጉት ነገር ልዩ መለያቸውን የሚያገኙ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት አሉ። የእነርሱ ክርስቲያናዊ አገልግሎት እና የድርጊት መርሃ ግብሮች ትልቁ ጥንካሬዎቻቸው ናቸው። ብዙውን ጊዜ ለአባሎቻቸው የሚደረጉ እና የማይደረጉ ረጅም ዝርዝሮች አሏቸው። በሚያሳዝን ሁኔታ ፣ እነዚህ ቤተ-እምነቶች ብዙውን ጊዜ የክርስትናን እምነት ወደ ድርጊት ብቻ ያወርዱታል። ክርስትና አንድ ነገር የማድረግ ጉዳይ ይሆናል። እና ይህ በድርጊት ላይ መጨነቅ ብዙውን ጊዜ ወደ ሕጋዊነት (ሕግ-አጥባቂነት) ይመራል።




በተግባር ላይ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት የምናስበውንና የሚሰማንን ነገር ችላ እንድንል ያደርገናል

> *በራሴ የክርስትና ሕይወት ውስጥ፣ በእርግጠኝነት መታዘዝ ላይ አፅንዖት እንዴት አስፈላጊ እንደሆነ አይቻለሁ። እኔ ማለቴ፣ ክርስቶስ እኛ ሄደን እርሱ ያዘዘንን ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማርን ደቀ መዛሙርት እንድናደርግ ወደ ዓለም ልኮናል፡፡ ስለዚህ መጀመሪያ አማኝ ስሆን፣ በእውነት ክርስቶስ ያስተማረውን መታዘዝ እና በተለይም ለታላቁ ተልእኮ መታዘዝን አጽንዖት በሚሰጥ በአማኞች ወይም ቤተ-እምነት ውስጥ አባል ነበርኩ። ግን ከጊዜ በኋላ ያ ዓይነት ትምህርት የጸጋ እና የፍቅር ስሜት እና ወንጌል የሚሰጠንን ነፃነት ጋረደብኝ፡፡ እግዚአብሔር የነገረኝን ነገር ብቻ በመታዘዝ የምኖር ቢሆን ኖሮ እስካሁን ለመኖር ኃይል አላገኝም ነበር፡፡ የፍቅር ስሜት ፣ የጸጋ ስሜት ፣ የመውደቅ የነፃነት ስሜት እንዲሁ አስፈላጊ ነው… ስለዚህ መታዘዝ የሚያስፈልገን ይመስለኛል። ሕይወታችንን እንዴት እንደምንኖር ልንጨነቅ ይገባናል ፣ ነገር ግን ወንጌል በሆነ መንገድ ነፃ አውጥቶናል ሕግን መጠበቅ ብቻ የማያስገኘውን ኃይል ሰጥቶናል፡፡*
>
> **— ቄስ ፍራንክ ሲንድለር**

ሦስተኛ ሌሎች ሥነ-መለኮታዊ ወጎች እራሳቸውን የሚለዩት በኦርቶዶክሳዊነት ወይም በኦርቶፕራክሲስ ላይ ባደረጉት ትኩረት ሳይሆን የበለጠ በኦርቶፓስነታቸው ነው።




Preoccupation with our emotions can lead us to neglect what we know and what we do.

## ኦርቶፓቶስ

በእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የክርስትና እምነት ስሜታዊ ልኬት ማዕከላዊ ደረጃ አለው። ሃይማኖታዊ ፍቅር በጣም ከፍ ያለ ከመሆኑ የተነሳ ብዙ ጊዜ ሌሎች ብዙ ነገሮች አስፈላጊ አይደሉም። እነዚህ ክርስቲያኖች በአስተምህሮ መጨነቅ አይፈልጉም። በተጨማሪም የደስታ ስሜት ለሚሰጡአቸው ተግባራት እንጂ ለሌሎች ድርጊቶች

ትኩረት የላቸውም፡፡ በዚህ ምክንያት ፣ እነዚህ ቤተ-እምነቶች በስሜታዊነት ተለይተው የሚታወቁ ናቸው፡፡

> *እኔ ያደግሁት በጉባኤ-እግዚአብሔር ትውፊት ውስጥ ነው፡፡ ጉባኤ-እግዚአብሔር በብዙ መንገዶች እኛ እንደ እግዚአብሔር አምሳል የተፈጠርነውን የስሜታዊነት ጎናችን ላይ ትኩረት የሚያደርግ ወግ አለው፡፡ ነገር ግን ለአንድ ነገር ዋጋ የሚሰጥ አካሄድ ለዚያ ነገር ከመጠን በላይ ዋጋ በመስጠት ሊሳሳት ይችላል፡፡ እኛ በአምላክ አምሳል የተፈጠርን ሁለንተናዊ ፍጡር መሆናችንን በጥቂቱ መገንዘብ የጀመርኩበት ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ነበር። ያ ስሜታዊ ብቻ ሳይሆን የእውቀት (ኮግኒቲቭ) እና ፈቃድ ያለን ሰዎች ነን፡፡ ያንን መገንዘብ ስጀምር እና መጽሐፍ ቅዱስ ስለእነዚህ ሶስት ማንነቶች የሚናገርበትን መንገድ ሳስተውል፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አእምሯችን እና በፍቃዳችን እና በስሜታችን መካከል ስላለው ግንኙነት እርስ በእርስ እንደሚደጋገፉ - ሲምባዮቲክ እንደሆነ እንደሚናገር ተረዳሁ፡፡ በእርግጥ ግንኙነቱ በሁለቱም መንገዶች ሊፈስ ይችላል ማለት ነው። አንዳንድ ጊዜ ስሜታችን የሚነሳው ከትክክለኛ አስተሳሰብ ነው። ግን በእውነቱ፣ አንዳንድ ጊዜ ትክክለኛ አስተሳሰብ ከፍልቀ-ስሜቶች፣ ከትክክለኛ ፍልቀ-ስሜቶች፣ ከትክክለኛ ስሜት ይነሳል። አንዳንድ ጊዜ ስሜታችን እንዴት እንደምንሠራ ያሳውቀናል። አንዳንድ ጊዜ የምንሠራበት መንገድ ስሜታችንን ያሳውቀናል። ስለዚህ እነዚህ ሦስቱ የእኛ ማንነቶች አንዱ ሌላውን ያሳውቃሉ እና ያ እኔ ማን እንደሆንኩ እና ሌሎች እንደ ስሜታዊ ፍጥረታት ማየት እንዳለብኝ ሚዛናዊ እንድሆን ረድቶኛል።*
>
> — ዶክተር ኤም ቢ

እያንዳንዱ ሰው የክርስትናን ወጎች ዝንባሌዎች በተለያዩ መንገዶች መገምገም አለበት ማለት አያስፈልገውም። ነገር ግን ሥነ-መለኮታዊ ወጎች ከእነዚህ አቅጣጫዎች አንዱን ወይም ሁለቱን በማጉላት በአጠቃላይ ማንነታቸውን ያገኛሉ ማለት ተገቢ ነው።

አሁን የክርስትና ወጎችን ሀሳብ ከገለፅን እና እንደዚህ ያሉ ወጎች ብዙውን ጊዜ የሚያሳዩትን ዝንባሌዎች አይተናል፣ ሥነ-መለኮታዊ ግንባታን በተመለከተ ለእነዚህ ትምህርቶች ሥነ-መለኮታዊ ወጎች ያላቸውን አስፈላጊነት መገንዘብ አለብን።

## የትውፊት አስፈላጊነት

ስለ ወጎች ግንዛቤ ማግኘት ሁለት ወሳኝ ሚናዎችን ይጫወታል፡፡ በመጀመሪያ ፣ ስለራሳችን የበለጠ እንድንረዳ ይረዳናል። ሁለተኛ ፣ ስለሌሎች የበለጠ እንድንረዳ ይረዳናል። ከሥነ-መለኮታዊ ወጎች አንፃር እራሳችንን እንዴት ማየት እንደምንፈልግ ለአፍታ እናስብ።

### ራሳችንን ለማወቅ

እስከ ቅርብ አሥርተ ዓመታት ድረስ መሪዎቹ ዓለማዊ ፈላስፎች እውነትን ለመፈለግ እራሳችንን ከባህላዊ ሰንሰለት፣ በተለይም ከሃይማኖታዊ ወግ ማላቀቅ አስፈላጊ እንደሆነ ይናገሩ ነበር። ይህ አመለካከት በምዕራባውያን ባህሎች ውስጥ በጣም ተደማጭ ሆነ፡፡ ከዚህም የተነሣ ስመ-ጥር የወንጌላውያን ክርስቲያኖች ጭምር አሳቡን ተቀብለውታል። በደንብ ለተመሰረተው ሥነ-መለኮታዊ ወግ ዋጋ ከመስጠት፣ እግዚአብሔር በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የገለጠውን እውነት ለመፈለግ ሁሉንም ትውፊቶች ወደ ጎን መተው እንዳለብን ታሰበ፡፡

ወጎች በእኛ ሥነ-መለኮት ላይ ተጽዕኖ ማሳደር የለባቸውም የሚለው ሀሳብ በብዙዎች የእውቀት ብርሃን ዘመናዊነት በጣም ተወዳጅ እና የተደገፈ አመለካከት ነበር። የእውቀት ብርሃን ዘመን ከሚባለው ወዲህ መጽሐፍ ቅዱስን በመደበኛ ትምህርት (የአካዳሚ ጥናት) ዓላማ ከሥነ-መለኮት አንድ ጎን አሳብና ወጎች የተፋታ ሆነ፡፡ የክርስትና እምነትን ምክንያታዊነት ለመጠበቅ የተደረገው ሙከራ የየዴካርት ዘዴ እንደነበር ማስታወስ አስፈላጊ ነው፡፡ ዴካርት ሁሉንም ነገር ይጠራጠራል፤ ከዚህም የተነሣ እውቀትን ከእምነት በግልፅ እንዲለይ አደረገ፡፡ እንደ አጉል እምነት እና ተራ ሃይማኖታዊ ወግ ያሉ እምነቶች ተጨባጭ እና ምክንያታዊ እውነትን በመከተል መወገድ ነበረባቸው።

አሁን በብዙ መንገዶች እራሳቸውን ከሃይማኖታዊ ቅርሶቻቸው ወይም ከተለየ የክርስትና ሥነ-መለኮታዊ ወግ ለመላቀቅ የሚሹ ተማሪዎች የእውቀት (ብርሃን) እና የካርቴሺያን መመዘኛዎችን ለሥነ -መለኮት መጠቀም ጀመሩ። በሚያሳዝን ሁኔታ ፣ ይህ ለሥነ-መለኮት አቀራረብ በቅርብ ምዕተ ዓመታት ውስጥ በምዕራቡ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ለታየው አብዛኛው ክህደት ተጠያቂ ነው። ዘመናዊ ሊበራሊዝም እነዚህን የዘመናዊነት የእውቀት ብርሃን አጀንዳ ለሥነ-መለኮት

ተግባራዊ የማድረግ ውጤት ነው። ግን ሥነ-መለኮታዊ ወነችን ለመቋቋም የተሻለ መንገድ አለ። ከሥነ-መለኮታዊ አቅጣጫዎቻችን እራሳችንን ለመፋታት ከመሞከር ይልቅ ለራስ-ግንዛቤ መጣር የበለጠ ይጠቅማል። በሌላ አነጋገር፣ ሥነ-መለኮት ስንገነባ በየጊዜው ስለሚነካንብን የማይዳሰስ ቅርስ የበለጠ ማወቅ ለእኛ ይጠቅመናል። ራስን ማወቅ ከእነዚህ ተጽዕኖዎች ውስጥ አንዳንዶቹን እንድንገመግም እና እንድንቆጣጠር ያስችለናል



የሥነ-መለኮት ታሪካዊ አመጣጣችንን ማወቅ ለሥነመለኮት ግንባታችን ይረዳናል

> እኛ የተለያዩ ባህሎችና ርዕዮተ-ዓለሞች ባሉበት ዓለም ውስጥ እንኖራለን፡፡ እኛ ባዶ ጭንቅላት ያለን ሰዎች አይደለንም፡፡ እኛ ባዶ ሰሌዳ አይደለንም። እኛ ብዙ የራሳችንን ቅድመ-ግምቶች፣ የራሳችንን ቅድመ-ሐሳቦች ይዘን ወደ ቅዱሳት መጻሕፍት እናመጣለን… ግን በብዙ ምክንያቶች ተጽዕኖ እንደሚደርስብን፤ የእኔ ቤተ እምነት ወይም ሃይማኖታዊ ያልሆኑ ነገሮች፣ የቀድሞ አስተምህሮዎቼ፣ ወላጆቼ፣ ጓደኞቼ መገንዘብ አስፈላጊ ነው፣ በአጠቃላይ ዓለም በሁሉም መንገዶች፣ በፋሽኖች ና ሁኔታዎች በመረጃ ይሞሉናል፡፡ እነዚያ ነገሮች ሁሉ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመተርጎም ስንሳ ተጽዕኖ ያሳድሩብናል፡፡ ስለዚህ ፣ ወደዚያ ስሄድ ፣ እንደገና ፣ በትሕትና መሄድ አለብን ፣ በአክብሮት መሄድ አለብን እና አንዳንድ ነገሮችን ለመለወጥ ምናልባት የራሳችንን የኃጢአት ተፈጥሮ እና የልባችንን ፍላጎት መረዳት አለብን። ስለዚህ አሁን ፣ በሀሳባችንና የመንፈስ ቅዱስ እንደሆነ በምናስበው መካከል ያለውን እንዴት መለየት እንችላለን? ስለዚህ ፣ የትርጓሜ መሣሪያዎችን እና ከምንም በላይ ፣ የቅዱስ አባታችንን ማክበር አለብን።
>
> — ዶ / ር ታዴዎስ ጄ. ጄምስ ፣ ጁኒየር

እራሳችንን ጥቂት ጥያቄዎችን መጠየቅ በጣም ጠቃሚ ነው። መጀመሪያ ፣ ቤት የምትሉት ቤተ-እምነት የትኛው ነው? ከሃይማኖት ወይም ከአንድ ዓይነት እንቅስቃሴ አንፃር ማሰብ ትችላላችሁ። መደበኛ ወይም መደበኛ ያልሆነ ማህበር ሊሆን ይችላል። ምናልባት ከአንድ በላይ ወግ ወይም ወነች ጥምረት ተከታዮች ሊትሆኑ ትችላላችሁ።

ከዚህ ባለፈ የወጋችሁ አጠቃላይ ዝንባሌዎች ምንድናቸው? የቤተ-እምነታችሁ በዋናነት ኦርቶዶክሳዊነትን፣ ኦርቶፕራክሲስን ወይም ኦርቶፓቶስን ያጎላል? በሌላ አነጋገር ፣ እናንተ በጣም የምትጨነቁት ለትምህርት ፣ ለተግባር ወይስ ለስሜት ነው? በእምነትታችሁ ውስጥ የሚያነሳሳችሁ ነገር ምንድነው? በክርስቶስ ያለህን ሕይወታችሁን የሚያነቃቃችው ምንድነው? እነዚህን መሠረታዊ ዝንባሌዎች ከለያችሁ በኋላ፣ እንደዚህ ያሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የወጋችሁን ባህሪ በበለጠ መለየት መጀመር ትችላላችሁ- ምን ዓይነት ትምህርቶች በጣም አስፈላጊ ናቸው? ለትኞቹ ድርጊቶች በጣም አፅንዖት ትሰጣላችሁ? ተቀባይነት ያላቸው ወይም ተቀባይነት የሌላቸው ስሜቶች የትኞቹ ናቸው? ለእነዚህ አይነት ጥያቄዎች መልስ መስጠት ሲትችሉ፣ የእራሳችሁን የክርስትና ሥነ-መለኮት ማሳደግና በእናንተ ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ነገሮችን መቆጣጠር ትችላላችሁ፡፡

አሁን የሥነ-መለኮታዊ ወነችን አስፈላጊነት ከግምት ውስጥ ስናስገባ ፣ ስለራሳችን ግንዛቤ እንዲሁም ወጎቻችን በእኛ ላይ የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም የእኛ ወነች በሌሎች ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ግንዛቤ ሊኖረን ይገባል።


## ሌሎችን መገንዘብ

ከሌሎች አማኞች ጋር ስለ ሥነ-መለኮት ስንወያይ ፣ የእኛ ማህበራት እና ወጎቻቸው በእኛ ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ሁል ጊዜ ማስታወስ አለብን።



ቪዲዮዎችን፣ የትምህርት መመሪያዎችና ሌሎች ግብዓቶችን ለማግኘት Thirdmill at thirdmill.org. ይመልከቱ.

እነርሱ የሚገኙበት ሥነ-መለኮታዊ ጅረት ስለእምነታቸው ብዙ ነገሮችን ሊያብራራ ይችላል። ይህ ማለት ሌሎች ክርስቲያኖች ከእኛ በጣም የተለየ አጀንዳ ሊኖራቸው ይችላል። የተለያዩ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች ፣ ጥንካሬዎች እና ድክመቶች ሊኖራቸው ይችላል። ስለሌሎች ይህንን በተገነዘብን ቁጥር፣ መስተጋብሮቻችን የበለጠ ፍሬያማ ሊሆኑ እና መከፋፈልን የበለጠ ማስወገድ እንችላለን፡፡



የሌሎች ክርስቲያናዊ ወገኖች በእነርሱ ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ ስንረዳ ተገቢ ያልሆኑ መከፋፈሎችን ማስወገድ እንችላለን

> *የሌሎች አማኞች ወይም የሌሎች አብያተ-ክርስቲያናት ሥነ-መለኮታዊ ወግ ግንዛቤ በጣም አስፈላጊ ነው፣ ምክንያቱም ዛሬ እንደምናየው ቤተክርስቲያን ቤተ-እምነታዊ በሆኑ ጉዳዮች ተከፋፍላለች፡፡ ብዙዎቹ ጉዳዮች ሁሉም ቤተ እምነቶች በሚስማሙበት ሳይሆኑ ከቤተ-እምነት ወጎች ጋር በተገናኙ ጉዳዮች ላይ ነው፡፡ በክርስቲያኖች መካከል እና በቤተ እምነቶች መካከል ፍሬያማ መስተጋብር እንዲኖረን ከፈለግን፣ የሌላውን ወግ ማወቅ እንዲሁም ያንን ወግ ማክበር በጣም አስፈላጊ ነው። ይህ የእነርሱን ወግ ማወቅ ብቻ አይደለም ፣ ግን አንዳንድ ጊዜ ለምን እነዚያ ወጎች እንዳሉ እና ለምን እንደሚያምኑ ማወቅ አስፈላጊ ነው… የሚያደርጉትን ለማክበር ብቻ ሳይሆን ለሁለቱም ወገኖች ትርጉም ያለው መስተጋብር እንዲኖራቸው መንገድ ሊከፍት ይችላል። ለሁለቱም ይጠቅማቸዋል፤ የእግዚአብሔርን ሥራ አብረው እንዲሠሩ እንዲሁም በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ አብረው ሥራ እንዲሠሩ ያደርጋቸዋል።*
>
> — ቄስ ዶ / ር ሃምፍሬይ አኮጊራራም

በክርስትና ሥነ-መለኮት ላይ ያለንን አመለካከት ከገለጽን እና ልዩ ሥነ-መለኮታዊ ወጎች ሥነ-መለኮትን በመገንባት ሂደት ላይ ምን ያህል ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ የማወቅ አስፈላጊነት ከተመለከትን ፣ ወደ ሦስተኛው ርዕሳችን ማለትም ወደ ተሃድሶው ወግ መዞር አለብን። ይህንን ትምህርት መማር አለብን ምክንያቱም እነዚህ ትምህርቶች ብዙውን ጊዜ ተሃድሶ ወይም ተሃድሶ ሥነ -መለኮት ተብለው በሚታወቁ ሥነ-መለኮታዊ አመለካከቶች ላይ ጥልቅ ተጽዕኖ ይኖራቸዋል።

## የተሐድሶው ትውፊት/ወግ

የሥነ -መለኮት ደራሲዎች እና መምህራን ስለ ሥነ-መለኮታዊ አመለካከቶቻቸው በተቻለ መጠን ክፍት መሆን እንዳለባቸው አምናለሁ። እንደ ባዶ ሰሌዳዎች ወደ ቅዱሳት መጻህፍት የምንሄድ መስሎ መታየት ማንንም አይጠቅምም። አንድን የተወሰነ የክርስትና ወግ ብቻ መታዘዝ የለብንም። ለቅዱስ ቃሉ ሙሉ ስልጣን እራሳችንን ለመገዛት ሁል ጊዜ መጣር አለብን። አሁንም ቢሆን ፣ ከዚህ ወይም ከዚያ ቤተ-እምነት ጋር በጥቂቱ የሚያይዘን ቅድሚያ የምንሰጣቸው ጉዳዮች ወይም አጽንዖቶች ይኖራሉ፡፡ መምህራን ይህ እውነት መሆኑን ሲቀበሉ ተማሪዎቻቸው ከእነርሱ ያነበቡትን ወይም የሰሙትን ለመገምገም የተሻለ ብቃት ይኖራቸዋል፡፡

የተሐድሶ ትውፊት ገጽታዎችን ለመዳሰስ ፣ ሦስት ጉዳዮችን - በመጀመሪያ ፣ የዚህ የቤተክርስቲያን ታሪካዊ አመጣጥ እና እድገቶች ፣ ሁለተኛ ፣ የተሃድሶ ሥነ -መለኮት ዝንባሌዎች እና ሦስተኛ አንዳንድ ሥነ -መለኮታዊ ልዩነቶችን እንመለከታለን። እስቲ የተሐድሶ ትውፊት አመጣጥ እና እድገቶች በመጀመሪያ እንመልከት።

## ታሪካዊ አመጣጡና ዕድገቶቹ

“የተሐድሶ ሥነ -መለኮት” የሚለው ቃል የመጣው በ16 ኛው መቶ ዘመን ከነበረው የፕሮቴስታንት ተሃድሶ ነው ፣ ነገር ግን የፕሮቴስታንት ተሃድሶ ውስጥ ብዙ የተለያዩ ሥነ-መለኮታዊ እንቅስቃሴዎች ይካተታሉ፡፡ በጣም ጉልህ ከሆኑት ቡድኖች መካከል በጀርመን ውስጥ ሉተራኖች ፣ ዙሪክ ውስጥ ዚዊንግሊያውያን እና በጄኔቫ ውስጥ ካልቪኒስቶች ነበሩ። ምንም እንኳን በሰፊው ሁኔታ ሦስቱን እንቅስቃሴዎች እንደ ተሃድሶ ብንናገርም ፣ “ተሐድሶ” የሚለው ቃል በዋነኝነት ለሦስተኛው ቡድን - በጆን ካልቪን ሥነ-መለኮት ተጽዕኖ ሥር የወደቁትን ፕሮቴስታንቶችን የሚያመለክት ነው፡፡

አሁን ይህ ቤተ-እምነት በየትኛውም መንገድ በጄኔቫ የተገደበ አልነበረም። በተሃድሶ ዘመን የተሐድሶ አብያተ ክርስቲያናት በጣም ወንጌል ያሰራጩ ስለነበረ በምዕራብ አውሮፓና ከዚያ አልፎ በሌሎች ሥፍራዎች ተሰራጭተዋል፡፡ ካልቪን ራሱ ፈረንሳዊ ነበር ፣ እና ብዙ ተማሪዎቹ የፈረንሳይ ሁጉኖትን እንቅስቃሴ በመምራት ረድተዋል፡፡ እነዚህ ወጣት አገልጋዮች በስራቸው የመጀመሪያዎቹ አስርት ዓመታት ውስጥ ብዙ ስደት ደርሶባቸዋል። ነገር ግን የጄኔቫ ሥነ -መለኮት በጣም ጠንካራ ከመሆኑ የተነሳ ብዙ ቁጥር ያላቸው ወጣቶች ቤተክርስቲያንን ለመትከል ወደ ፈረንሳይ አገር ይሄዱ ነበር፡፡




በፕሮቴስታንት ተሐድሶ ውስጥ የነበሩ ሦስቱ ትልልቅ እንቅስቃሴዎች

የተሐድሶ እንቅስቃሴ በመላው አውሮፓ ማደጉን ቀጥሏል። በጀርመን፣ በፈረንሣይ፣ በቤልጂየም፣ በሆላንድ፣ በሃንጋሪ እና በሌሎች አገሮች ውስጥ በሺዎች የሚቆጠሩ አብያተ ክርስቲያናት ተተከሉ። ስለቀደሙት አህጉራዊ ተሃድሶ ሥነ-መለኮት በርካታ ትልልቅ ነጥቦችን መጠቀስ ይቻላል። ለምሳሌ በ1561 የቤልጂክ ንስሐ እና በ 1563 በሄይድልበርግ ካቴኪዝም በቤተክርስቲያኑ ተሃድሶ ውስጥ ትልቅ ትርጉም አላቸው። እነዚህ በጄኔቫ ይሰጡ ከነበሩ የሥነ-መለኮታዊ ሥርዓቱ ቀደምት አቀራረቦች ጥቂቶቹ ነበሩ። በተጨማሪም በአህጉር አውሮፓ ውስጥ የተሃድሶው ወግ አንድ ጠንካራ ክንድ የሆላንድ ተሐድሶ ቤተክርስቲያን ነበር። የአርሚኒያን ውዝግብ ለመቋቋም ከ 1618 እስከ 1619 የተሰበሰበው የዶርት ሲኖዶስ የታወቀ ነው - በአርሚኒየስ ትምህርቶች ላይ የተመሠረተ ውዝግብ ላይ የተካሄደ ስብሰባ ነበር፡፡ እነዚህ ከካልቪኒዝም ወጣ ያለ እይታ የነበራቸው ነበሩ፡፡

> *የቤተክርስቲያኒቱ ተሃድሶ ቅርንጫፍ ቀደምት ካቴኪዝም አንዱ ሄይድበርግ ካቴኪዝም ነው። ያንን ካቴኪዝም እወደዋለሁ ምክንያቱም ስለ ተሃድሶ ሥነ-መለኮት ብዙ ጊዜ የማይጎላ ነገርን ያሳያል። የተሃድሶ ሥነ-መለኮት አንዳንድ ጊዜ እንደ ከፍተኛ የአስተምህሮ የእምነት ስብስብ ተደርጎ ይቆጠራል እና በእውነቱ ስለ ተግባራዊ ሕይወት እና ስለ ክርስቲያኖች የዕለት ተዕለት ተሞክሮ አይመለከትም። ነገር ግን የሄይድልበርግ ካቴኪዝም በዚህ መንገድ ይጀምራል - “በህይወት እና በሞት ውስጥ ብቸኛው ምቾትህ ምንድነው?” በህይወት እና በሞት ውስጥ ብቸኛው ምቾትህ ምንድነው? ያ ካቴኪዝም በተጻፈበት ጊዜ የተሐድሶ ክርስቲያኖች በስደት ውስጥ ነበሩ፡፡ ይህ ካቴኪዝም በዚያ አውድ ውስጥ እንደተጻፈ ማወቅ*

**አለብን፡፡ በብዛት ስለ እምነታቸው እየሞቱ ነበር። የሚጠበቀው በስደቱ እንደሚቀጥሉ እና በእምነታቸው ምክንያት፣ ላመኑባቸው አቋሞቻቸው ምክንያት በብዛት መሞታቸውን እንደሚቀጥሉ ያስቡ ነበር። የዚያ ካቴኪዝም መከፈት - በዚህ የቤተክርስቲያን ውስጥ ቀደምት ከሆኑት አንዱ - "በህይወት እና በሞት በየትኛው መጽናኛ ታገኛለህ?" የሚለውን ጥያቄ እንደሚጠየቁ መገንዘቡ በጣም አስደናቂ ነው። በእርግጥ መልሱ በኢየሱስ፣ እግዚአብሔር አብ በራስህ ላይ ያሉትን ፀጉሮች እንኳን ስለሚያውቅ፤ ከእርሱ እንክብካቤ እና በሕይወትህ እንዲሆን እርሱ ከሚፈቅደው ውጭ ምንም ነገር ሊደርስብህ አይችልም። ግን ቢያንስ በመጀመሪያዎቹ ደረጃዎች እና ከዚያ በኋላ እንኳን ይህ የቤተክርስቲያን በኦርቶፓቶስ ወይም በእምነታችን ውስጥ የስሜቶች ሚና በጣም የተጨነቁ መሆኑን መገንዘብ አስደናቂ ነገር ነው።**

**— ዶ/ር ሪቻርድ ኤል ፕራት ፣ ጁኒየር**

የተሐድሶው ወግ በብሪታንያ ደሴቶች ላይም በከፍተኛ ሁኔታ አደገ። ከ 1505 እስከ 1572 የኖረው ጆን ኖክስ በጄኔቫ ተምሮ በስኮትላንድ የተሃድሶ ወይም የፕሬስባይቴሪያን አብያተ ክርስቲያናትን ለማቋቋም ተመለሰ። የ 1560 እስኮትስ መግለጫ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የታወቀ ሰነድ ነው። ተሐድሶው እንዲሁ በእንግሊዝ ውስጥ ሥር ሰደደ ፣ ፒዩሪታኖች ከሌሎች ቡድኖች ጋር በመሆን በ 1646 የዌስትሚኒስተር የእምነት መግለጫን አዘጋጅተው በ 1647 እና ትልቁ እና አጭሩ ካቴኪዝም ታተመ፡፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች በ 1648 ተጨምረዋል። እነዚህ ሰነዶች የዌስትሚንስተር ልኬቶች/ደረጃዎች ፣ ዛሬም በብዙ ተሃድሶ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ጥቅም ላይ እየዋሉ ናቸው። በብሪታንያ ደሴቶች ውስጥ ያሉ ብዙ የተለያዩ የባፕቲስት ቡድኖች እራሳቸውን እንደ ተሐድሶ ወግ አካል አድርገው በመቁጠር በመጀመሪያ በ 1644 በታተመው እንደ ለንደን ባፕቲስት መግለጫ ባሉ ሰነዶች ላይ እምነታቸውን ገልጸዋል።

የተሐድሶው ወግ በብዙ የዓለም ክፍሎችም ተሰራጨ። የእንግሊዝ ቲዩሪታኖች እና በኋላ የስኮትላንድ ፕሬስቢቴሪያኖች ፣ ወደ ሰሜን አሜሪካ በኃይል አምጥተውታል። የሚስዮናዊነት ጥረቶች ወደ ብዙ የአፍሪካ ክፍሎች ፣ ኢንዶኔዥያ ፣ ደቡብ ምሥራቅ እስያ እና ደቡብ አሜሪካም ሄደዋል፡፡

በታሪኩ በእያንዳንዱ ደረጃ ፣ የተሃድሶ ሥነ-መለኮትን ልዩ ባህሪያቱን እንዲያገኝ ያደረጉ ብዙ እድገቶች ነበሩ። እንደ ሌሎቹ የቤተክርስቲያኗ ቅርንጫፎች ሁሉ በተሃድሶ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ከባድ ውድቀቶች እና ክህደት ተከስተዋል። ችግሮች አሁንም ይህንን የክርስቶስ አካል ክፍል ይጎዳሉ። ዛሬ ግን ሕያው፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድምፅ ያለው የተሃድሶ ሥነ-መለኮት በሁሉም የዓለም ክፍሎች ማለት ይቻላል እየተሰጠና ሰዎችም እየኖሩበት ይገኙሉ፡፡

አሁን ስለ ተሃድሶው የቤተክርስቲያን ቅርንጫፍ ታሪካዊ አመጣጥ እና እድገቶች ትንሽ ስላወቅን ሥነ-መለኮታዊ ዝንባሌዎቹን እንመልከት።

## ዝንባሌዎች

በዚህ ትምህርት ቀደም ብለን፣ የክርስትና ወጎች ጥንካሬዎች ቢኖራቸውም ድክመቶች እንዳሏቸው ጠቁመናል። በእውነቱ ፣ ብዙውን ጊዜ ትልቁ ጥንካሬያችን ትልቁ ድክመታችን ይሆናል። እንደምናውቀው ፣ ቀደም ሲል ታላላቅ መሪዎች እና ተሚጋቾች እንኳ ሰብዓዊ ድክመቶች ነበሯቸው። በእኛ ወቅታዊ ሁኔታ ውስጥም ተመሳሳይ ነው። ስለዚህ ይህንን ተከታታይ ትምህርት የሚመራው የሥነ -መለኮታዊ ጅረት አዎንታዊ እና አሉታዊ ዝንባሌዎች ምንድናቸው?

በክርስቲያናዊ ወጎች ውስጥ ስለ ዝንባሌዎች ቀደም ሲል ከተወያየንበት አንፃር ፣ የተሃድሶ ሥነ -መለኮት ምሁራን በጣም ዋጋ የሚሰጡት ምን እንደሆነ መጠየቅ አለብን -ኦርቶዶክስ ፣ ኦርቶፕራክሲስ ወይም ኦርቶፓቶስ? ባለፉት መቶ ዘመናት በአንዳንድ ያልተለመዱ ሁኔታዎች ፣ የተሃድሶው ወግ በዋነኛነት በኦርቶፕራክሲስ ላይ አፅንዖት መስጠቱ ግልፅ ነው። ከአንዳንድ የፒዩሪታን ጽሑፎች በስተቀር ፣ ኦርቶፓቶስ ብዙም ትኩረት አላገኘም።

አስተምህሮ እና ተግባር ኦርቶፓቶስን በተጨባጭ እስኪያገልል ድረስ አፅንዖት በሚሰጥበት ጊዜ ፣ በትምህርቱ ላይ ያለን አፅንዖት ወደ ምሁራዊነት እና ተግባራዊነት ደግሞ ወደ ሕግ-አጥባቂነት ይመራል፡፡ ኦርቶዶክስ እና ኦርቶፕራክሲስ የተሃድሶ ሥነ-መለኮት ተፈጥሯዊ ዝንባሌዎች ናቸው፡፡ ሁለቱም ለዚህ የክርስቶስ አካል ጥንካሬዎች እና ድክመቶች ናቸው። ስለዚህ ፣ ለበጎም ሆነ ለከፉ ፣ እነዚህ ትምህርቶች በዚህ ወግ ተጽዕኖ ስለነበራቸው ፣ እነዚህ ዝንባሌዎች በእነዚህ ትምህርቶች ውስጥ እንደ ጥንካሬዎች እና ድክመቶች ደጋግመው ይታያሉ።

የተሐድሶውን ወግ አመጣጥ እና ዝንባሌዎች ከተመለከትን ፣ አንዳንድ በጣም የታወቁ የአስተምህሮ ልዩነቶችን ማየት አለብን - በተለይም ይህ ወግ በሌሎች ሥነ -መለኮታዊ ገጽታዎች ላይ ተጽዕኖ ስለሚኖረው። እነዚህን ባህሪዎች መረዳት በእነዚህ ትምህርቶች ውስጥ የቀረቡትን አመለካከቶች በበለጠ ለመገምገም ይረዳል።

## ልዩ መገለጫዎች

ይህንን የቤተ-እምነቷን የአስተምህሮ አቋሞችን ከዚህ በመቀጠል እንጠቅሳለን - በመጀመሪያ ፣ የተሃድሶው "አምስት ብቻዎች" ተብሎ የሚታወቀው ነገር ነው:: ሁለተኛ የቅዱሳት መጻሕፍት አንድነት ፤ ሦስተኛ ስለእግዚአብሔር ያለው አስተምህሮ ሲሆን አራተኛው በክርስትና እና በሰው ባህል መካከል ስላለው ግንኙነት የተለየ አቀራረብ ናቸው:: እስቲ በመጀመሪያ በየተሃድሶ ሥነ-መለኮት አምስቱ ብቻዎችን እንመልከት።

### አምስቱ ብቻዎች

ከ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ስለ አምስቱ ብቻዎች (ሶላዎች) ማውራት የተለመደ ሆኗል። እነዚህ መሠረተ ትምህርቶች በተለምዶ "ሶላ" የሚለውን ቃል በሚይዙ መግለጫዎች ውስጥ ተጠቃለዋል ፣ እነርሱም "ለብቻ" ወይም "ብቻ" ማለት ነው። አብዛኞዎቹ ወንጌላውያን ቢያንስ ከእነዚህ ውስጥ አንዳንዶቹን ሰምተዋል - ሶላ ስክሪፕቱራ ፣ እርሱም "ቅዱሳት መጻሕፍት ብቻ" ማለት ነው ፤ ሶሎ ክሪስቶ ፣ "ክርስቶስ ብቻ"; ሶላ ፍዴ ፣ "እምነት ብቻ"; ሶላ ግራቲያ ፣ "ፀጋ ብቻ"; እና ሶላ ዲኦ ግሎሪያ ፣ "ክብር ለእግዚአብሔር ብቻ" ናቸው።

*ሶላ ስክሪፕቱራ* መጽሐፍ ቅዱሱ ብቸኛው የማይሳሳት የእምነት እና የሕይወት ሕግ ነው የሚለው ትምህርት ነው። በቤተክርስቲያን ጉባኤዎች ወይም በሊቀ ጳጳሱ በኩል ሊገለጽ የሚችል ከቅዱሳት መጻሕፍት ውጭ ቤተክርስቲያን ራሷ የማይሻር ወግ አላት ከሚለው የሮማ ካቶሊክ እምነት በተቃራኒ የቆመ ነው።

*ሶሎ ክሪስቶ* በእግዚአብሔር እና በሰው መካከል ብቸኛው መካከለኛ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ያረጋግጣል። ይህ ወደ ቅዱሳኖች ወይም ወደ ማርያም ለምልጃ የሚመለከቱትን የሚቃረን ነው። ክርስቶስ ብቸኛ አዳኝ ነው ፣ ኃጢአተኞች ከኃጢአት ይቅርታ እንዲያገኙ ፣ እና ከእግዚአብሔር ቁጣ የሚያመልጡበት ብቸኛው መንገድ ነው።


*ሶላ ፍዴ* ፣ ወይም "እምነት ብቻ" ፣ እግዚአብሔር አማኞችን የሚያጸድቀው በእምነት ብቻ ነው ፣ በሌላ መንገድ ለምሳሌ እንደ ሰው ጥረት ወይም የሰው *ሥራዎች* አይደለም።

*ሶላ ግራቲያ* ፣ "ጸጋ ብቻ" ፣ እግዚአብሔር የመዳንን በረከቶች የሚሰጠንበትን መንገድ ይገልጻል። እግዚአብሔር ለመረጣቸው ሰዎች ጸጋን ከዘላለም ጀምሮ ይሰጣል። እርሱ በክርስቶስ *ሥራ* መሠረት እኛን በነፃነት ያጸድቀናል እናም የእርሱ ጽድቅ ለእኛ ተቆጥሮልናል::

ሶላ ግራቲያ ለድነታችን አስተዋፅኦ የሚያበረክት የግል በጎነት እንደሌለን ያረጋግጣል። ከዘላለማዊ ምርጫ እስከ ዘላለማዊ ክብር የመዳን አጠቃላይ ሂደት በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ ብቻ የተመሠረተ ነው።

*ሶሊ ዲኦ ግሎሪያ*፣ ትርጉሙ "ክብር ለእግዚአብሔር ብቻ" ማለት ፣ በፍጥረት ውስጥ ሁሉም ፍጥረታት እና ድርጊቶች ለእግዚአብሔር ብቻ ክብርን ለማምጣት የተፈጠሩ ናቸው ብሎ የሚያምን ትምህርት ነው። የተሐድሶ አራማጆች ይህንን መፈክር የተጠቀሙት ለሰብአዊ ፍጡራን የተወሰነ ክብር መስጠትን የሚደግፉ አስተምህሮዎች ሁሉ በመቃወማቸው ነው ፣ እንዲህ ዐይነቱ አስተሳሰብ ለእግዚአብሔር ብቻ የሚገባውን ክብር ማሳጣት ነው::

ከሶላዎች በተጨማሪ ፣ የተሃድሶው ወግ ሌላ ልዩ መለያ በብሉይ እና በሐዲስ ኪዳን አንድነት ላይ ያለው አመለካከት መሆኑን ልብ ማለት አስፈላጊ ነው።





**የቅዱሳት መጻሕፍት አንድነት**

በቅርብ ታሪክ ውስጥ በሰሜን አሜሪካ ላሉ ብዙ ወንጌላውያን እና በእነርሱ ተጽዕኖ ሥር ለሚመጡ ፣ በብሉይ ኪዳን እና በአዲስ ኪዳን መካከል መሠረታዊ መለያየት አለ ብሎ ማመን የተለመደ ሆኗል። ብሉይ ኪዳን በአጠቃላይ እንደ ሕግ ፣ አዲስ ኪዳን ደግሞ እንደ ወንጌል ይታያል። ብሉይ ኪዳን ሥራን እንደሚያጎላ ይታሰባል ፣ ነገር ግን አዲስ ኪዳን ጸጋን ያጎላል። ብሉይ ኪዳን ፍርድን ብቻ እንደሚያመጣ ይታሰባል ፣ አዲስ ኪዳን ግን ድነትን ያመጣል።

በአንጻሩ ፣ የተሐድሶው ወግ መላውን መጽሐፍ ቅዱስ እንደ አንድ የተዋሃደ ሥነ -መለኮት እንደሚያቀርብ ይመለከታል። ሕግ በብሉይ ኪዳን እና በአዲስ ኪዳን ውስጥም አለ። ወንጌል በሁለቱም ኪዳናት ውስጥ አለ። በሁለቱም ኪዳናት መልካም ሥራዎች ያስፈልጋሉ። መለኮታዊ ጸጋ በሁለቱም ኪዳናት መዳንን ያመጣል። በብሉይም ሆነ በሐዲስ ኪዳን ፍርድ አለ ፣ እና መዳን በአዲስም ሆነ በብሉይ ኪዳን ይመጣል። አሁን በርግጥ ፣ በሁለቱ ኪዳናት መካከል ልዩነቶች አሉ ፣ ግን እነዚህ ልዩነቶች የዕድገት ልዩነቶቸ ናቸው። ይህም ማለት ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ እምነት እድገቶችን ከቀዳሚ ደረጃዎች እስከ ኋላ ደረጃዎች ይወክላሉ። ግን በብሉይና በሐዲስ ኪዳናት መካከል መሠረታዊ ሥነ -መለኮታዊ አንድነት አለ።



ቪዲዮዎችን፣ የትምህርት መመሪያዎችና ሌሎች ግብዓቶችን ለማግኘት Thirdmill at thirdmill.org. ይመልከቱ.




ብዙ ዘመናዊ ወንጌላውያን በብሉይ እና በሐዲስ ኪዳናት መካከል መሠረታዊ መለያየት እንዳለ ያምናሉ።


ብዙ ጊዜ ለክርስቲያኖች ሳናግር ብሉይ ኪዳን እና አዲስ ኪዳናት ስለ እግዚአብሔር እና ስለ ወንጌል የሚናገሩት መንገድ ፍጹም የተለያዩ እንደሆኑ የሚመስል ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ ባሳለፍኩ ቁጥር ለእኔ እና ለሌሎችም የበለጠ ግልፅ እየሆነ ይሄዳል፣ በእርግጥ ብሉይ ኪዳን እና አዲስ ኪዳን በአንድ ድምፅ ይናገራሉ። ወደ ኤማሁስ በሚወስደው መንገድ ላይ ፣ ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን ፣ የሕግ ፣ የነቢያት ፣ የጥበብ መጻሕፍትን ፣ ሁሉም ስለ እርሱ ፣ ስለ ወንጌል እና ስለ ወንጌል አንድምታዎች በግልፅ እንደሚናገሩ ለደቀመዛሙርቱ ገለፀላቸው። ስለዚህ አጠቃላይ የመጽሐፍ ቅዱስ አወቃቀር የተመሠረተው እግዚአብሔር በጸጋ ለሰው ልጅ በሚሠራበት ሥራ ላይ ነው ፣ በዚያ ጸጋ ብርሃን ፣ እንደ እኛ ያሉ ሰዎች ለእርሱ ምላሽ በመስጠት ለእርሱ ትዕዛዛት በመታዘዝ እና ሕይወት እንዲኖሩ ይጠራል፡፡ በመጨረሻ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ውበት የሆነውን ያንፀባርቃል። ስለዚህ ብሉይ ኪዳንን እና አዲስ ኪዳንን ሳነብ በአንድ ድምፅ ሲናገሩ እሰማለሁ። እግዚአብሔር የሚሰጣቸው ትዕዛዛት ከክርስቶስ በፊት እና በኋላ ለጊዜ እና ለቦታ የተቀረፁ እና የተስማሙ ቢሆኑም ፣ ሁሉም የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዲሆን የሚፈልጉት ነገር ተመሳሳይ ነው፡፡

— ዶ/ር ጂ ጋሪ ሚላር

በብሉይ እና በሐዲስ ኪዳናት መካከል ያለውን ልዩነት በትክክል ስናጤን ፣ በዌስትሚኒስተር የእምነት መግለጫ በምዕራፍ 7 ክፍል 6 ላይ እንዲህ ይላልe -

በተለያዩ አስተዳደሮች ሥር አንድ ብቻ እንጂ በአይነት የሚለያዩ ሁለት የጸጋ ቃል ኪዳኖች የሉም።

ይህ በቅዱሳት መጻሕፍት አንድነት ላይ አፅንዖት መስጠት በተሃድሶ ሥነ-መለኮት ውስጥ አንዳንድ ስህተቶችን አስከትሏል። አንዳንድ ጊዜ በብሉይ ኪዳን እና በአዲስ ኪዳን መካከል በቂ ልዩነት አይደረግም። ሆኖም ፣ ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ አንድነት ላይ አፅንዖት መስጠት ከተሃድሶ ሥነ -መለኮት ታላቅ ጥንካሬዎች አንዱ ነው። በእነዚህ ትምህርቶች ውስጥ የእኛን ሥነ-መለኮት እንዴት እንደምንገነባ ስንመረምር ፣ ከአዲስ ኪዳን የበለጠ ፣ ብሉይ ኪዳንን እንደ ብዙ እንጠቀማለን። ግባችን ከአዲስ ኪዳን ጋር ብቻ ሳይሆን ከመላው መጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚስማማውን ሥነ -መለኮት መገንባት ይሆናል። በእነዚህ ጥናቶች ላይ የተሐድሶው ወግ ተፅእኖ በሁሉም አቅጣጫ ማለት ይቻላል በዚህ መንገድ ይገለጣል።




የተሐድሶ ሥነ -መለኮት በሐዲስ ኪዳን መካከል መሠረታዊ ሥነ -መለኮታዊ አንድነት ያየል እና ማንኛውንም ልዩነቶች በቀላሉ እንደ ዕድገት ይቆጥራል።

በሦስተኛ ደረጃ ፣ በሶላና በቅዱሳት መጻሕፍት አንድነት ላይ ከማተኮሩ በተጨማሪ፣ የተሃድሶ ሥነ-መለኮት ስለእግዚአብሔር ላለው ትምህርትም ልዩ ትኩረት ይሰጣል።

## ስለእግዚአብሔር ያለው አስተምህሮ

> *ፕሮቴስታንቶች አሁን ለ 500 ዓመታት አጥብቀው ሲናገሩ ስለእግዚአብሔር አስተምህሮ በራሱ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ሁሉም አስተምህሮዎች ስለእግዚአብሔር አስተምህሮ አንጻር መታየት አለባቸው ይላሉ፡፡ የፕሮቴስታንት ስለእግዚአብሔር አስተምህሮ ከምሥራቅ ኦርቶዶክስ ወይም ከሮማ ካቶሊክ ስለእግዚአብሔር አስተምህሮ በይዘቱ በእጅጉ የተለየ አይደለም። ሆኖም የተለየ የፕሮቴስታንት አስተምህሮ ነው ምክንያቱም ፕሮቴስታንቶች እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ሁሉ ስለእግዚአብሔር አስተምህሮ አንጻር መታየት እንዳለበት ያምናሉ። ስለዚህ ሥነ -መለኮት ተገቢነት ነው- የሥነ-መለኮት ምሁራን ስለእግዚአብሔርን አስተምህሮ ብለው ይጠሩታል - ለእያንዳንዱ አማኝ አስፈላጊ ነው፡፡ እያንዳንዱ አማኝ ራሱን እንደ ሥነ-መለኮት ምሁር አድርጎ ቢያስቡም ባያስብም ስለእግዚአብሔር አስተምህሮ አለው። ያ ስለእግዚአብሔር አስተምህሮ የክርስትና ሕይወታቸውን የሚመሩበትን መንገድ ይወስናል፡፡*
>
> — ዶክተር ጄ ሊጎን ዱንካን III

ከታሪክ አኳያ ፣ የተሐድሶ ሥነ -መለኮት ለሁለቱም የእግዚአብሕር ባሕሪያት መለኮትና ሕልውና ትኩረት ይሰጣል፡፡ እንደ ዌስትሚኒስተር የእምነት መግለጫ ያሉ የተሻሻሉ መመዘኛዎች ስለእግዚአብሔር ዘላለማዊ የመለኮት ድንጋጌዎች እና ስለእግዚአብሔር ስለማይቀረው የእግዚአብሔር ስጦታ በጥብቅ ይናገራሉ። ይህ በተሃድሶ ሥነ -መለኮት ውስጥ ያለው ታሪካዊ ሚዛናዊነት መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን ከሁሉ የላቀ (መለኮት) እና ሕልውና ያለው መሆኑን የሚገልጽ ነው። በአንዳንድ ምንባቦች ውስጥ እርሱ ከፍ ያለ ፣ ሩቅ ፣ ከሁሉም በላይ ሆኖ ተገልጾአል። በሌሎች ምንባቦች ውስጥ ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ እርሱ እንደ ሕያው ፣ ቅርብ እና ወዳጅ ከታሪክ ጋር የተዛመደ ፣ በተለይም ከሕዝቡ ጋር አብሮ እንደሚሆን ይናገራሉ።

እንደዚያም ሆኖ ፣ ከሌሎች የክርስትና ወጎች ጋር ሲነጻጸር ፣ የተሐድሶ ሥነ-መለኮት ዝንባሌ የእግዚአብሄርን ልዕለ - እምነት (የበላይነት) ላይ አፅንዖት ለመስጠት ነው። ሌሎች የክርስትና ወጎች ብዙውን ጊዜ እንደ ደግነቱ ፣ ምሕረቱ ፣ ፍቅሩ እና ርህራሄው ፣ ትዕግስቱ እና በአብሮዎቱ ያሉ በቀላሉ ከእግዚአብሔር ቅርበት ጋር የሚዛመዱ መለኮታዊ ባህሪያትን ያጎላሉ። የተሃድሶ ሥነ-መለኮት እነዚህን መለኮታዊ ባሕሪትን ይቀበላል፣ ነገር ግን ከዘለአለማዊነቱ ፣ የማይለወጥ መሆኑ፣ ሉዓላዊነቱ ፣ ራሱን ችሎ በመኖሩ፣ ሁሉን ቻይነቱን ፣ እና በሁሉ ቦታ መገኘቱ ና የመሳሰሉትን የመጉላት አዝማሚያ አለው።

ለምሳሌ ፣ የዌስትሚኒስተር አጭሩ ካቴኪዝም በባህሪው የተሻሻለውን የእግዚአብሔርን ትርጉም ያዳምጡ። ለጥያቄ ቁጥር 4 መልስ:

እግዚአብሔር ማንነው?

ካቴኪዝም በዚህ መንገድ ይመልሳል-

እግዚአብሔር መንፈስ ነው ፣ በማንነቱ ፣ በጥበቡ ፣ በኃይሉ ፣ በቅድስናው ፣ በፍትህው ፣ በጥሩነት እና በእውነት ማለቂያ የሌለው ፣ ዘላለማዊ እና የማይለወጥ ነው።፡

ይህ መልስ እውነት እና በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት ነው። ነገር ግን በግልጽ የሚያሳየው የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ባሕሪያትን - እነዚያን ባሕሪያት ከሁሉም በላይ ያደርጉታል፤ እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር አብሮ ቢሆንም፡፡

ምንም እንኳን በእግዚአብሄር የበላይነት ላይ አፅንዖት ማድረግ ወደ ጽንፍ ሊወሰድ ቢችልም ፣ ስለ እግዚአብሔር የበላይነት (መለኮትነት) ትክክለኛ ግንዛቤ በብዙ የክርስትና ሥነ -መለኮት ክፍሎች ውስጥ በትክክል ይገኛል። ስለዚህ ፣ ይህ ዝንባሌ እነዚህን ትምህርቶች በልዩ አቅጣጫዎች ይመራቸዋል።

ከሶላዎች ፣ ከቅዱሳት መጻሕፍት አንድነት እና ከእግዚአብሔር ትምህርት ጋር ፣ የተሐድሶው ቅርንጫፍ አንድ የመጨረሻ ልዩ መለያ መጥቀስ አለብን። የተሃድሶ ሥነ -መለኮት በክርስትና እና በሰው ባህል መካከል ያለውን ግንኙነት እንዴት ይመለከታል?

## የሰው ባሕል

*እኔ የተሃድሶ ሥነ-መለኮት በእግዚአብሔር እና በሰው ባህል መካከል የጠበቀ ግንኙነትን ያያል ብዬ አምናለሁ። በሌላ አነጋገር… እግዚአብሔር በማንኛውም ባህል ፣ በማንኛውም ዕድሜ ውስጥ ሁል ጊዜ የሚገለጥ መሆኑን ሁል ጊዜ ማግኘት ትችላላችሁ። በሰው ሕይወት ውስጥ ፣ በሰው ባህል ውስጥ የእግዚአብሔር መገኘት አስፈላጊ እና ሁል ጊዜም ግልፅ ነው። ታላቅ ምሳሌ የሚሆነው ሐዋርያው ጳውሎስ በአቴንስ ሄዶ ሲሰብክ እና አቴናውያን የሚያመልኩትን "ያልታወቀውን አምላክ" ሲያይ ፣ ያንን አጋጣሚ ተጠቅሞ "እኔ የምሰብከላችሁ አምላክ ይህ ነው" ብሎ ሲነግራቸው ነው። በእግዚአብሄር አያምኑም በሚሉ ባህሎች ውስጥ እንኳን እግዚአብሔር ሲንጸባረቅ ማየት ትችላላችሁ ፣ ምክንያቱም በሥነ ምግባር መርሆዎቻቸው ውስጥ አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔርን መገኘት ማየት ትችላላችሁ፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለማየት ፣ የእግዚአብሔርን ፍጥረት ማየት ትችላላችሁ። ቢክዱትም እንኳ በእግዚአብሔር እና በሰው ባህል መካከል ሁል ጊዜ የጠበቀ ግንኙነት አለ።*

— ቀሲስ ፓብሎ ቶረስ ፣ ትርጉም

በጄኔቫ ከሚገኘው የካልቪን አገልግሎት ዘመን ጀምሮ ፣ የተሐድሶው ወግ ለእነዚህ ጉዳዮች ሚዛናዊ ወጥነት ያለው አካሄድ ወስዷል። ይህንን የተለየ አመለካከት ለማጠቃለል አንደኛው መንገድ በሪቻርድ ኒቡሩ ክርስቶስ እና ባህል በተሰኘው መጽሐፋቸው የፈጠረውን የታወቀ የአጻጻፍ ዘይቤ መከተል ነው። ኒቡሩር በመጽሐፉ ውስጥ የተለያዩ ክርስቲያናዊ የባህል አቀራረቦችን በአምስት ትላልቅ ቡድኖች ሰብስቧል።

"ክርስቶስ ከባህል ጋር የሚቃረን" - ኒቡሩር ይህን ቃል የተጠቀመው ባህል ክፉ ነው እና ክርስቲያኖች ከባህል መራቅ አለባቸው የሚለውን አመለካከት ለመግለት ነው። እንደ የመካከለኛው ዘመን የገዳም ትዕዛዞች እና ዘመናዊ የአሚሽ እና ሜኖናይት ማህበረሰቦች ያሉ የመለየት እንቅስቃሴዎች የዚህ አመለካከት ምሳሌዎች ናቸው።

ኒቡሩር ባሕልን በዋናነት የሚቀበሉትንና ክርስቶስን በባሕል ውስጥ ቦታ የሚሰጡትን አመለካከቶች ለማሳየት "የባህል ክርስቶስ" የሚለውን አገላለጽ ይጠቀማል። ይህ አቀራረብ በብዙ ዘመናዊ ሊበራል ፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ይታያል።

በሁለቱ የክርስቶስ ከባሕል ጋር የሚቃረን እና የባህል ክርስቶስ ጽንፎች መካከል ፣ ክርስቶስ እና የሰውን ባህል ለማስታረቅ የተለያዩ መንገዶችን የሚሞክሩ ሦስት አመለካከቶችን ይገልጻል። “ክርስቶስ ከባህል በላይ” በክርስቶስ እና በዓለም መካከል ውህደትን የሚሞክር እይታ ነው። “ክርስቶስ እና ባህል በፓራዶክስ” በክርስቶስ እና በአለም መካከል የሚለው አመለካከት ደግሞ ሁለቱም የሚቃረኑ የሚመስሉ ግን አብሮ መኖር የሚችሉ መሆናቸውን የሚገልጽ አሳብ ነው፡፡ “የባህል ለዋጩ ክርስቶስ” ክርስትና ተጽዕኖ ሊያሳድርበት ይገባል ፣ እና በአንዳንድ መንገዶች ባህሎችን ወደ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመዘኛዎች ይለውጣል። በኒቡሩ እይታ ፣ የተሃድሶው አቀማመጥ ከዚህ ከመጨረሻ ምድብ ጋር ይጣጣማል።

በተለያዩ ጊዜያት ፣ የተሐድሶው ወግ ይህንን አመለካከት በተለያዩ መንገዶች በተግባር ላይ አውሏል። በሚያሳዝን ሁኔታ ፣ ከእነዚህ ጥረቶች መካከል አንዳንዶቹ ከአውሮፓ ቅኝ ግዛት ጋር በቅርበት የተቆራኙ ነበሩ። ግን ከዚህ ቀደም በአጠቃላይ የትራንስፎርሜሽን ሞዴሉ አንዳንድ አዎንታዊ ምሳሌዎች ነበሩ። ብዙውን ጊዜ ፣ ክርስቶስ የሰውን ባሕል እንዲቀይር ለማድረግ የተደረገው ሙከራ የበለጠ አዎንታዊ ምሳሌዎች ፣ የእንግሊዙ ፕዩሪታንና የአሜሪካው ፕዩሪታን እንዲሁም በሆላንድ ውስጥ የአብርሃም ኩይፐር ጥረቶችን ማንሳት እንችላለን፡፡ በሁሉም ክስተቶች ፣ በባህል ላይ ያለው አጠቃላይ የተሃድሶ አቋም በዚህ መንገድ ሊጠቃለል ይችላል - እግዚአብሔር መጀመሪያ ሰብአዊነትን ሲፈጥር እና በኤደን ገነት ውስጥ ባስቀመጠን ጊዜ ለሰው ልጅ የባህል ስልጣን ሰጠው። የዘፍጥረት 1:28 የታወቁትን ቃላት ያዳምጡ -

> እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው። ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም፤ የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው። (ዘፍጥረት 1:28).

አዳምና ሔዋን ምድርን እና እምቆቸዋን በማስተዳደር በዓለም ላይ እንደ እግዚአብሔር ምክትል ገዥዎች ሆነው በማገልገል ለእግዚአብሔር ክብር እንዲያመጡ ተጠርተዋል። ከተሃድሶው አንፃር ይህ ባህላዊ ተልእኮ ችላ አልተባለም፡፡ ይልቁንም በተቀረው የቅዱሳት መጻሕፍት ተረጋግጧል። በእርግጥ ፣ ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን የሰጠው የወንጌል ተልእኮ ይህ ባህላዊ ተልእኮ እንዲፈፀም የእግዚአብሔርን ህዝብ ከኃጢአት ለመዋጀት የተነደፈ ነው።

በዚህ ምክንያት ፣ የተሃድሶ ሥነ -መለኮት እያንዳንዱ የሕይወት ልኬት በክርስቶስ ጌትነት ሥር መሆን እንዳለበት ያምናል፡፡ የተሃድሶ ሥነ -መለኮት አንዳንድ የሕይወት ገጽታዎች ሃይማኖታዊ ፣ ሌሎች ደግሞ ዓለማዊ ናቸው የሚለውን ሀሳብ አይቀበልም። ከዚህ አንፃር ፣ ሕይወት ሁሉ ሃይማኖተኛ ነው ፣ በእውነተኛ ወይም በሐሰት ሃይማኖት የሚገዛ ነው። ሥነ -ጥበባት ፣ ሳይንስ ፣ ሕግ ፣ ፖለቲካ ፣ ንግድ ፣ ቤተሰብ ፣ ትምህርት ቤት ፣ እያንዳንዱ የሰዎች ባህል ገጽታ የእግዚአብሔርን ቃል በሚያከብር እና ለእግዚአብሔር ክብር በሚያመጡ መንገዶች መከናወን አለበት።

> *በብዙ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የእግዚአብሔር መንግሥት በእያንዳንዱ የማንነታችን ክፍል እና በምንሠራው እያንዳንዱ ሥራ ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር እና የእግዚአብሔርን ንግሥና ለማንፀባረቅ እንደ ምስል ተሸካሚዎች ያለን ሚና የደቀ መዝሙርነት አስፈላጊ አካል መሆኑ በጣም ግልፅ ነው። . በኤፌሶን 4 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ “ክርስቶስን ማወቅ” ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይናገራል። ስለ ደቀመዝሙርነት ሲናገር ፣ በአምልኮ ልምምዶች አይጀምርም። ይልቁንም ለጎረቤቶቻችን በምንናገርበት መንገድ ይጀምራል ፣ ውሸትን መናገር ትተን ለጎረቤቶቻችን እውነትን መናገር እንጀምር። ከዚያ ዜጋ የመሆን ሚና - ወደ የሥራ ህይወታችን ይሄዳል ፣ “የሰረቀ መስረቅ ያቁም እና ለሌሎች የሚሰጥ ነገር እንዲኖረው በእጆቹ ይሠራል” ይላል። ስለዚህ ፣ “ክርስቶስን ከመማር” ወይም የክርስቶስ ደቀ መዝሙር ከመሆን አንፃር ማየት የምንችለው እያንዳንዱን የሕይወታችን ክፍል መንካቱ ነው። በዚያ ምዕራፍ ውስጥ እና ወደ ምዕራፎች 5 እና 6 ፣ ስለ የቤተሰብ ሕይወት ፣ ወላጆች እና ልጆች ፣ ባሎች እና ሚስቶች ይናገራል። ስለ አምልኮ ሕይወታችን እና እርስ በእርስ በመዝሙር መበረታታት እንዳለብን ይናገራል። ለአለቆች እና ለባለስልጣኖች እንዴት ምላሽ መስጠት እንዳለብን ይናገራል። ኢየሱስ ምሳሌዎቹን በተናገረ ጊዜ ይህንንም አድርጓል። እርሱ የተወሰነ የሕይወት ክፍልን ብቻ መጠቀሙ ነበር - ይህንን ሀብታም እና ድሃውን ተመልከቱ - የእግዚአብሔር መንግሥት ምን እንደምትመስል ይናገር ነበር። ሀብታሞች ከድሆች ጋር እንዴት ይዛመዳሉ? ስለዚህ እያንዳንዱ የሕይወታችን ክፍል በእግዚአብሔር መንግሥት ሥር ነው።*
>
> — ዶክተር ግሪጎሪ አር

# ማጠቃለያ

በዚህ የክርስትና ሥነ -መለኮትን ለመመርመር ዓላማ ባደረገው በዚህ ትምህርት ውስጥ ፣ ይህንን አጠቃላይ ጥናት የሚመሩ አንዳንድ አስፈላጊ እይታዎችን አዘጋጅተናል። በመጀመሪያ የክርስትናን ሥነ -መለኮት ከሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ጋር የሚስማማ ነው ብለን ገለጽነው። እንዲሁም የተለያዩ የቤተክርስቲያን ቅርንጫፎች የሚቀርጹ እና የሚለዩ የተለያዩ የክርስትና ወጎች በሥነ -መለኮት ውስጥ እንዳሉ አይተናል። በመጨረሻም ፣ እነዚህ ትምህርቶች አመጣጥ እና እድገቶችን ፣ ዝንባሌዎችን እና ሥነ-መለኮታዊ ልዩነቶችን ጨምሮ በተሃድሶው ወግ አቅጣጫዎች እንደሚመሩ ጠቁመናል።

እያንዳንዱ የክርስቶስ ተከታይ የክርስትናን ሥነ -መለኮት የመመርመር መብት ተሰጥቶታል። እኛ ስናደርግ፣ በአስተሳሰባችን፣ በምግባራችን እና በስሜታችን ከሌሎች አማኞች ጋር ብዙ የሚያመሳስለንን እናገኛለን - በእኛ ኦርቶዶክስ ፣ ኦርቶፕራክሲስ እና ኦርቶፓቶስ ውስጥ ማለት ነው። ግን እኛ ደግሞ የክርስትና ሥነ -መለኮት ያለ ልዩነት እንዳልሆነ እንመለከታለን። በሺህ ዓመታት ውስጥ የተለያዩ የቤተክርስቲያን ቅርንጫፎች የየራሳቸውን ትውፊት፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን እና አጽንዖቶችን አዳብረዋል። ከእነዚህ ወጎች ጋር ስንገናኝ ስፍር በሌለው መንገድ እንጠቀማለን። በእያንዳንዱ የሕይወት ልኬት ውስጥ ክርስቶስን የሚያከብር ሥነ -መለኮት ለመገንባት ስንፈልግ የክርስትናን ሥነ -መለኮት ማሰስ ከእያንዳንዱ አማኝ ጋር የምንጋራው የዕድሜ ልክ ጥረት ነው።



ቪዲዮዎችን፣ የትምህርት መመሪያዎችና ሌሎች ግብዓቶችን ለማግኘት Thirdmill at thirdmill.org. ይመልከቱ.

# አስተዋፅዖ አድራጊዎች

**Vincent Bacote, Ph.D. (Host)** is Associate Professor of Theology and Director of the Center for Applied Christian Ethics at Wheaton College. Dr. Bacote holds an M.Div. from Trinity Evangelical Divinity School with an emphasis on Urban Ministry, and an M.Phil. and Ph.D. in Theological and Religious Studies from Drew University. He is a member of the American Academy of Religion, the Christian Theological Research Fellowship and the Evangelical Theological Society. A prolific writer and speaker, Dr. Bacote has authored and edited numerous books, including *The Spirit in Public Theology: Appropriating the Legacy of Abraham Kuyper* (Baker Academic, 2005) and *The Political Disciple: A Theology of Public Life* (Zondervan, 2015). He is also a regular columnist for *Comment* and has contributed to magazines such as *Books and Culture*, *Christianity Today*, and *Think Christian*. He and his family reside in the Chicago area.

---

**Rev. Dr. Humphrey Akogyeram** is a professor at Good News Theological Seminary in Accra, Ghana.

**Dr. M. B.** is professor at Bethlehem College and Seminary.

**Dr. David R. Bauer** is Dean of the School of Biblical Interpretation and the Ralph Waldo Beeson Professor of Inductive Biblical Studies at Asbury Theological Seminary.

**Dr. Steve Curtis** is Director of Timothy Two Project International.

**Dr. James K. Dew, Jr.** is Assistant Professor of the History of Ideas and Philosophy at Southeastern Baptist Theological Seminary.

**Dr. J. Ligon Duncan III** is Chancellor and CEO of Reformed Theological Seminary and the John E. Richards Professor of Systematic and Historical Theology.

**Dr. Thaddeus J. James, Jr.** is Vice President of Academic Affairs at Birmingham Theological Seminary.

**Dr. Kelly M. Kapic** is Professor of Theological Studies at Covenant College.

**Dr. Craig S. Keener** is the F.M. and Ada Thompson Chair of Biblical Studies at Asbury Theological Seminary.

**Dr. Scott Manor** is Assistant Professor of Historical Theology, Vice President of Academic Affairs, and Dean of Faculty at Knox Theological Seminary.

**Dr. J. Gary Millar** is Principal of Queensland Theological College and Founding Council Member of The Gospel Coalition, Australia.

**Dr. Andrew Parlee** serves as a missionary with Greater Europe Mission and as a member of the Faculty Board of Approval for Thirdmill.

**Dr. Gregory R. Perry** is Vice President for Strategic Projects at Thirdmill and former Associate Professor of New Testament and the Director of City Ministry Initiative at Covenant Theological Seminary.

**Dr. Richard L. Pratt, Jr.** is Co-Founder and President of Thirdmill.

**Dr. Tim Sansbury** is Assistant Professor of Philosophy and Theology and Vice President of Administration at Knox Theological Seminary.

**Rev. Frank Sindler** is a theological educator in Africa.

**Rev. Vuyani Sindo** is a lecturer at George Whitefield College in South Africa.

**Rev. Pablo Torres** is Pastor of Iglesia La Viña in Orlando, FL.

**Dr. Oliver L. Trimiew** is Associate Professor of Interdisciplinary Studies and Chair of Interdisciplinary Studies Department at Covenant College

# GLOSSARY

**የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ** - መሠረታዊ የክርስትና ሥነ -መለኮት መሰረታዊ መርሆችን ለማዋሃድ የተቀረፀ እና የተፃፈ የክርስትና እምነት መግለጫ (ከ 2 ኛ እስከ 6 ኛው ክፍለዘመን ገደማ)

**አርሚኒየስ ፣ ያዕቆብ-(1560-1609)** የቅድመ ምርጫ/ዕጣ ፈንታ አስተምህሮን ጨምሮ የካልቪኒዝም ዋና ዋና አስተምህሮዎችን ለመቃወም ያደገው የደች የሃይማኖት ምሁር።

**ቤልጂካል መግለጫ** - በ 1561 በኔዘርላንድ በሪፎርመር ጊዶ ደ ብሬስ የተፃፈ የእምነት መግለጫ; ከተሐድሶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ደረጃዎች አንዱ ነው፡:፡

**ካልቪን ፣ ዮሐንስ-** (1509-1564) የክርስትና ሃይማኖት መሠረቶች የሚል የፃፈው ፈረንሳዊው የሃይማኖት ምሁር እና ቁልፍ የፕሮቴስታንት ተሃድሶ አራማጅ የነበረ።

**ካቶሊክ** - ትርጉሙ "ሁለንተናዊ"; በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ ቤተ ክርስቲያንን ሁሉንም አማኞች ፣ ከየቦታዎች፣ በታሪክ ዘመናት ሁሉ ያካተተች አድርጎ ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ነው፡፡

**ባህላዊ ተልእኮ** - በዘፍጥረት 1 28 ላይ ያለው ትእዛዝ የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን ክብር ለማሳየት ፍጥረትን እንዲያዳብር እና እንዲገዛ የሚያስተምር

**ዴካርትስ ፣ ሬኔ-** (1596-1650) ፈረንሳዊ ፈላስፋ እና የሂሳብ ሊቅ; ብዙውን ጊዜ "የዘመናዊ ምክንያታዊነት አባት" ተብሎ ይጠራል

**መለኮታዊ ሕልውና/አብርዖት** - ከሰውና ከፍጥረታት ጋር ያለውን ቅርበት የሚያመለክት የእግዚአብሔር ባህሪ ፣ በቦታ እና በጊዜ ውስጥ የእግዚአብሔር ንቁ ተሳትፎ

**ዶክትሪን** - በሥነ -መለኮታዊ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎች ውህደት እና ማብራሪያ

**ስሜታዊነት** - ያልተመጣጠነ እና ብዙውን ጊዜ በስሜቶች ላይ ከመጠን በላይ ትኩረት

**ትምህርተ-ብርሃን-** በሃይማኖታዊ ፣ በማህበራዊ እና በፖለቲካ ወጎች ላይ የሰውን ምክንያት ያጎላ የ 17 ኛው እና የ18ኛው መቶ ዘመን የፍልስፍና እንቅስቃሴ

**ሄይድበርግ ካቴኪዝም** -የአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን የፕሮቴስታንት እምነት የቅዱሳት መጻሕፍትን ትምህርቶች አንድ ላይ አጠቃልሎ ለማቅረብ የተፃፈ

**ሁጉኖትስ** - በተሃድሶው ወቅት ስደት የደረሰባቸው እና ከፈረንሳይ ለመሸሽ የተገደዱ የፈረንሣይ ፕሮቴስታንቶች

**አእምሯዊነት** - ስሜታዊ ወይም የባህሪ ሀሳቦችን ከግምት ሳያስገባ በእውቀት ላይ ያልተመጣጠነ ትኩረት መስጠት

**ጆን ኖክስ-** (እ.ኤ.አ. 1505-1572) በስኮትላንድ ውስጥ የተሃድሶ ወይም የፕሬስቢቴሪያን አብያተ ክርስቲያናትን ያቋቋመው የስኮትላንድ ተሃድሶ አራማጅ

**አብርሃም ኩይፐር-** (1837-1920) የደች የሥነ-መለኮት ምሁር ፣ ጸሐፊ እና የኔዘርላንድ ጠቅላይ ሚኒስትር ለግል ትምህርት ትኩረት የሰጠ እና በኔዘርላንድ ውስጥ የተሃድሶ አብያተ ክርስቲያናትን ያቋቋመ።

**ሕግ-አጥባቂነት** - እምነትን ወይም የክርስቶስን ወንጌል ከግምት ሳያስገባ የሞራል ሕጉን ለመጠበቅ ወይም ለማክበር ያልተመጣጠነ ትኩረት መስጠት

**ለንደን ባፕቲስት መግለጫ** - ለመጀመሪያ ጊዜ በ 1644 የታተመ ለካልቪኒስት ባፕቲስቶች የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የፕሮቴስታንት ማጠቃለያ። ሁለተኛው የለንደን መግለጫ በ 1677 ታትሞ በ 1689 እንደገና ታተመ

**ማርቲን ሉተር-(1483-1546)** በ1517 በዊትበርግ ቤተክርስቲያን በር ላይ ተሐድሶውን የጀመረው የ 16 ኛው ክፍለ ዘመን የጀርመን መነኩሴ እና የፕሮቴስታንት ተሃድሶ አራማጅ።

**ኒቡሩር ፣ ኤች ሪቻርድ-** (1894-1962) ክርስቶስን እና ባሕልን የጻፈው አሜሪካዊ የሃይማኖት ሊቅ እና መምህር

**ኦርቶዶክስ** - ትክክለኛ ወይም ቀጥተኛ አስተሳሰብ

**ኦርቶፓቶስ - ትክክለኛ ስሜቶች ወይም ፍለቀ-ስሜቶች**

**ኦርቶፕፕክሲስ** – ትክክለኛ ተግባር ወይም ልምምድ

**የፕሮቴስታንት ተሐድሶ-** በአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን ለማስተካከል የሞከረ የሃይማኖት እንቅስቃሴ ፣ ግን በመጨረሻ ተለያይቶ የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያንን አቋቋመ።

**የተሃድሶ ሥነ-መለኮት** - የካልቪኒስት ሥነ-መለኮት ትምህርት ቤት በአምስቱ ሶላዎች ፣ በእግዚአብሔር ታላቅነት ፣ በቅዱሳት መጻሕፍት አንድነት እና ስልጣን ፣ እና በባህል መለወጥ ላይ አፅንዖት የሚሰጥ

**እስኮትስ መግለጫ** - ጆን ኖክስን ጨምሮ በ1560 በስኮትላንዳዊያን አገልጋዮች የተፃፈው የመጀመሪያው የስኮትላንድ ተሐድሶ ቤተክርስቲያን።

**ሶላ ፍዴ** - "እምነት ብቻ" የሚል ትርጉም ያለው የላቲን ሐረግ; መጽደቅ በሥራ ሳይሆን በእምነት ብቻ ነው ብሎ ማመን ፤ ከተሃድሶ መሰረታዊ መርሆዎች አንዱ ነው

***ሶላ ግራቲያ*** - "ጸጋ ብቻ" የሚል ትርጉም ያለው የላቲን ሐረግ; መዳን የተመሠረተው በእግዚአብሄር ጸጋ ላይ ብቻ እንጂ በግል ብቃታችን ላይ አይደለም የሚል እምነት ፤ ከተሃድሶ መሰረታዊ መርሆዎች አንዱ ነው፡፡

***ሶላ ስክሪፕቱራ*** - የላቲን ሐረግ ትርጉም "ቅዱሳት መጻሕፍት ብቻ"; ቅዱሳት መጻሕፍት የሁሉም ሥነ -መለኮታዊ ጥያቄዎች የበላይ እና የመጨረሻ ዳኛ እንደሆኑ ይናገራል። ከተሃድሶ መሰረታዊ መርሆዎች አንዱ ነው፡፡

***ሶሊ ዲኦ ግሎሪያ*** - የላቲን ሐረግ ትርጉም "ክብር ለእግዚአብሔር ብቻ"; ሁሉም ፍጥረታት እና ድርጊቶች ለእግዚአብሔር ብቻ ክብርን ለማምጣት የተነደፉ ናቸው ብሎ ማመን ፣ ከተሃድሶ መሰረታዊ መርሆዎች አንዱ ነው፡፡

**ሶላ ክርስቶ** – የላቲን ሐረግ ትርጉም "ክርስቶስ ብቻ"; በእግዚአብሔር እና በሰው መካከል ብቸኛው መካከለኛ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ብሎ ማመን; ከተሃድሶ መሰረታዊ መርሆዎች አንዱ ነው

**የሃይማኖት ቅይጥ/ማመሳሰል** - የተለያዩ ሃይማኖቶችን የመቀላቀል ወይም ፍልስፍና ከሃይማኖት ጋር የመቀላቀል ልምምድ

**የዶርት ሲኖዶስ-** በ1618-1619 በኔዘርላንድ የተሐድሶ ቤተክርስቲያን ስብሰባ ፣ በአርሚኒያ ውዝግብ ላይ ተከራክረው ለአምስቱ የካልቪኒዝም ነጥቦች ውሳኔ ወስነዋል።

**ሥነ -መለኮታዊ ወግ** - በአንጻራዊ ሁኔታ ሲታይ የቆየ ሥነ -መለኮታዊ ትምህርት ፣ ልምምድ ወይም ስሜት ሆኖ አንዱን የቤተክርስቲያን ከሌላው የሚለይ

**ባህላዊነት** - ሥነ-መለኮታዊ እምነቶችን መሠረት ያደረገው ከቅዱሳት መጻሕፍት ይልቅ ለቆዩ ባህላዊ ምርጫዎች ትኩረት መስጠት

**ዌስትሚኒስተር የእምነት መግለጫ** – በዌስትሚኒስተር ኡቭ መለኮታዊ ጉባኤ ተሰብስቦ በ 1647 የታተመ ሥነ -መለኮታዊ ትምህርታዊ ማጠቃለያ

**ዌስትሚኒስተር ትልቁ ካቴኪዝም** – ባህላዊው የፕሮቴስታንት ማጠቃለያ የክርስትና ትምህርት፣ በመጀመሪያ በ1647 የታተመ። ከአጭሩ ካቴኪዝም የበለጠ ማጠቃለያ ነው

**ዌስትሚኒስተር አጭሩ ካቴኪዝም** – ባህላዊው የፕሮቴስታንት ማጠቃለያ የክርስትና ትምህርት ፣ በመጀመሪያ በ1647 የታተመ

**ኡልሪክ ዝዊንግሊ**-(1484-1531) የስዊስ ፕሮቴስታንት መስራች ተደርገው የሚቆጠር ተፅዕኖ ፈጣሪ የስዊስ ተሃድሶ እና ቄስ ነበር፡፡